የመለስ ራዕይ

ኤርምያስ ለገሰ

ዋጋ 450-500

የመለስ ራዕይ

ሙሉአለም የሚዘርፍበትን ሁኔታ ሲያፈላልግ አንድ ጓደኛውን ያገኛል።ጓደኛው ሊረጅም ጊዜ ተከማችቶ እየዛገ ያለውን እና ጉበረትነቱ የጉና የሆነ ላሜራ በማማሸ ዋጋ እንዲገዛው ያስማማል። በምትኩም 40ሺህ ኩንታል ሲምንቶ ለየር ባየር እንዲወስድ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት በወራት ውስጥ ራሱን እና ጓደኛውን በሚሊየነር ጐራ እንዲሰለፉ ያደርጋል።

እንደ አውነቱ ከሆነ ሰብሀት ነጋ እና ሙሉአለም ብርሀኔ የተቃናጁበት ዝርፊያ እና የአየር በየር ንግድ በወሬ የሚነገር አይደለም። በህወሓት ፓሊት ቢሮም ሆነ በኤፈርት አመራሮች ዘንድ ለሰምንታት ግምገማ የተካሄደበት ነው። ፈጻሚዎቹም ድርጊቱን መፈፀማቸውን እምነዋል። ነገር ግን የሀግ ተጠያቂነቱ ከመጣ እነሱ ብቻ ላይሆን በሀገሪቱ ሰው ሰራሽ የሲምንቶ እጥረት ያስከሰቱትም አብረው መጠየቅ እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተውበታል።

***

ወደ ጌታቸው በላይ ስንመለስ ደግሞ አዜብ የወሰደችው እርምጃ ወደ አሰር ከማምራቱ በፊት ሀገር ጥሎ ጠፋ። ህወሓት ከቃኙ ተደናገጠች።

የሰብሀት ወጉብም ተሰበረ። በእሱ ያልተጠበቀ እርምጃ ምክንያት ሽማግሌው ሰብሀት የወይዘሮ አዜብ መቀለጃ ሆነ። ባገኙት አጋጣሚ እንገቱን ማስደፋት ስራዬ አድርጋ ተያያዘችው። በኤፈርት ውስጥ የዘረጋውን ኔትወርክ ለመበጣጠስ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላት። ተራ በተራ እየጠረገች አወጣቻቸው። አቅማቸው ካሷ በታች እንደሆነ አርግጠኛ የሆነችባቸው እንደ ታጋይ አተይ ታደለ አይነት ሰዎች ብቻ ተወች።

ጌታቸው በላይን በተመለከተ በየጊዜው የሚጉላሉብኝን ጥያቄዎች ሳላነሳ መሄድ ልቤ አልፈቀደም። ይህ ሰው የህወሓት ገሹ መደብ አካል በመሆን የማእከላዊ ኮሚቴና ፓሊት ቢሮ አባል ነበር። በአቶ መለስ ካቢኔ ውስጥ በሁለት የተለያዩ ተቋማት ሚኒስትር በመሆን ተሳትፏል። የንግድ ኢምፓየር የመሰረተው ትዕምት ሁለተኛ ሰው ነበር። የዚህን ተቋም የዝርፊያ ስትራቴጂ ለማስፈፀም በግንባር ቀደምትነት የተንቀሳቀሰ ሰው ነው።

ከህወሓት ለሁለት መሰንጠቅ በኋላ የህወሓት ካድሬዎች ሰርአቱን ጠጋግኖ ከሚያስቀጥሉ ሰዎች ግንባር ቀደም አድርገው ይወስዱት ነበር። በዚህም ምክንያት "ጌቾ ከአዜብ እንጂ ከህወሓት

አልተሳኩታምና" አስከማለት ደርሰዋል። በአዲሱ አንጋገር ደግሞ "ጌቾ ሞላ አስግዶም ነው" የመሃሰለው አይነት ነው። ሞላ አስገዶምና ...ደረጃ በደረጃ!!

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አሜሪካን ኢምግሬሽን ቢሮ ሁሉ እውነቱን ከጌታቸው በላይ እፍ መባማት ይፈልጋል። መብትም አለው። በግብርና ጉምሩክ አገልግሎት ለአፈርት ሲሰራ የነበረውን ላቦታጅ ማጋለጥ አለበት። ገቢዎችና ጉምሩክ በወሳኝ የሀሳፊነት ቦታዎች ላይ ለምን ህወሓትን እንደሚመድቡ መናገር ይጠበቅበታል። አዲሰ ከሚቀጠሩ ወጣቶች ውስጥ የእንበሳው ድርሻ ለምን ለትግራይ ልጆች እንደሚሰጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ከእሱ አንደበት መስማት ይፈልጋል።

አቶ መለስ በምርጫ 97 ማግሰት ባቋቋመው ስውር መንግስት ውስጥ ኢኮኖሚ ዘርፉን ለመቆጣጠር ከተመደቡት ቁልፍ ሰዎች አንዱ ነበር። የፓለቲካና ፀጥታ ጥምር ኮሚቴ አባል በመሆን በየቀኑ ግምገማ ይቀመጥ ነበር። በግድያ የተሰማሩ የመከላከያ፣ የደህንነትና ፌደራል ፓሊሶችን በስምና በተሳትፎ ደረጃቸው አብጠርጥሮ ያውቃል።እስከማውቀው ድረስ በምርጫ 97 አቶ መለስ በአዲስ አበባ ባደራጀው ማዘዣ ጣቢያ ውስጥ በአመራርነት ተሳትፏል። ቡሀላይም በላፍቶ ክፍለከተማ የተፈፀሙ ወንጀሎች በእሱና በአሁኑ ሰአት የአዲሰ አበባ ስራ አስኪያጅ የሆነው ሀይሌ ፍስሀ መሪነት የተፈፀሙ ናቸው። ጌታቸው በቀጥታ በአዲስ አበባ የተፈፀሙ ወንጀሎችና ግድያዎች ተሳታፊ ነው።

ጌታቸው በላይ በምርጫ 97 የተወዳደረው ከቅንጅቱ ሊቀመንበር ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል ጋር ነበር። በተወዳደረበት ላፍቶ ክፍለ ከተማ የተፈፀሙ ወንጀሎችን እሱና በወቅቱ የክፍለከተማው ከንቲባ የነበረው ሀይሌ ፍስሀ አመራር ሰጪነት የተተገበሩ ናቸው። በኢህአዴግ ቢሮ በሚደረጉ ግምገማዎች ክፍተኛ የበቀል ስሜት ከሚታይባቸው የህወሓት ካድሬዎች በግንባር ቀደም የሚለለፉት አንዱ ነበር። "ንበረት ወደ ቀበሌ፣ ትግሬ ወደ መቀሌ" የሚለውን በራሳቸው የተፈበረከ ፕሮፓጋንዳ የአዲሰ አበባ ህዝብ ሲናገር ሰምቻለሁ በማለት ምስክርነት በተደጋጋሚ ሲሰጥ ተመልክቻለሁ። ያለማጋነን ጌታቸው በላይ ብዙ የሚያውቀው ነገር አለ። ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ የትግራይ ተወላጆች በፍሎሪዳ፣ በኮለራዶ፣ በቬጋስና ዋሽንግተን ዲሲ በጅምላ ጋዝ ማደያና የመጠጥ ግሮሰሪ ውስጥ የሚሳተፉበት የገንዘብ ምንጭ ከየት እንደሆነ ያውቃል። በአጅ አዙር ተሳትፎም ይጠረጠራል።

(በዚሪ ጊታቸው በላይ የፓለቲካ ጥያቄዎች ጠይቆ በፍሎሪዳ ግዛት ጃክሰንቪል ከተማ ይኖራል። በአካባቢው የሚኖሩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ቀርበው ሊያናግሩት ምክረዋል። ስውየው ፀብ ያለው ከአቶ መለስና ባለቤቱ ጋር አንጂ ከሰርአቱ ጋር አንዳልሆነ አረጋግጠዋል። ምንም ነገር ለመናገር ፍቃደኛ አንዳልሆነ ግን ደግሞ የአቶ መለስን ምት አንዳየ ሁሉ የእቴጌ አዜብን ሙድምት በአጭር ጊዜ አንደሚመለከት ለምነት አለው። በዙሪያው የተሰባሰቡትና በአጭር ጊዜ የመርካታ ጋዝ ማደያ ባለቤት መሆን የቻሉት የሀገሩ ሰዎች አንዲያግዙት ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል። ለይለው ፍቃደኛ አልሆነም።)

***

ስዬና ገብሩ

ስዬ ምን አለ?

ከህወሐት አባልነት ከተባረሩ በኋላ ዘለግ ያለ መጽሀፍ ለመጻፍ ከደፈሩት ሠዎች ግንባር ቀደም የሆኑት ስዬ አብርሃ እና ገብሩ አስራት ናቸው። ስዬ "ነፃነትና ጽኝነት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የአሱ እና የቤተሰቦቹን የከሰ ሂደት የሚያሳይና የሚሞግት ባለ 440 ገጽ መጽሐፍ ጽፏል። የከሱ መሠረታዊ ምክንያት ሴብነት ስለመፈፀሙ ሳይሆን ፖለቲካዊ እንደሆነ ለማስረዳት ጥረት አድርጓል። በተለይም ከአቶ መለስ ጋር "በኢትዮ- ኤርትራ" ጦርነት ዙሪያ ልዩነት ሰለነበረው በሙስና እሱና ቤተሰቦቹ ሠለባ እንደሆኑ ይገልጻል። አቶ መለስ በሕግ ፋንታ የህይል መንገድ በመምረጥ ህወሐትን መሠንጠቁን፣ ...ፌደራሊዝምን የልጅ ጨዋታ ማድረጉን፣ ...በመከላከያ ሠራዊቱና በህወሐት መካከል ልዩነት እንዳይኖር ማድረጉን፣ ...የጄኖከራሲና የፍትሕ ተቋማት የሆኑትን ምርጫ ቦርድ፣ ፍርድ ቤት፣ የፀጥታ ተቋማቱና ፖሊስ በራሱ ቁጥጥር ስር እውሱ እንደፈለገ ሲያደርጋቸው እንደሚውልና እንደሚያደር አመላክቷል።

ስዬ መለስን በተመለከተ እንዲህ ይለናል፣

"አቶ መለስ ሲከራከር ለመርህ እና ለውነት ብዙም አይጨነቅም። በመቅቱ ሊያዘው ከርከር ትንሸም ቢሆን ይረዳናል ብሎ ካመነ መርህን እና ለውነትን ገልብጦ የሚያነብ ከርከር ያመጣል። ዛሬ ለያዘው መከራከሪያ ይጠቅመኛል ካለ ትላንት የተናገረውን ገልብጦ እና ቀይሮ ይከራከራል" በማለት ወቅሶታል።

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ አቶ ስዬ አብርሃ ኤፈርትን በተመለከተ እንዴት እንደተመሠረተ፣ ለምን አላማ ታስቦ እንደሆነ እና የኤፈርት ጉዞን በተመለከተ በሁለት ገፅ (337-

338) ላይ በቅንጭቡ ለመዳሰስ ሞክሯል። በዚህ ነጠላ ኤፈርት በዋናነት የተሠማራባቸው ዘርፎች በሀገሪቱ ፍትሃ ብሔር ህግ መሠረት መቋቋሙንና የህዉሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በማእቀፉ ተከፋፍለው ሲመሩት እንደነበር በአጭሩ አሳይቷል።

ስዩ ኤፈርት በ1988 ዓ.ም. እንደተቋቋመና በምን ዘርፍ እንደተሰማራ በሚከተለው መልኩ በገጽ 337 ላይ፣

"ኤፈርት ሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ በህወሓት (TPLF) ሊድ የቆየውን ግምቱን ማወቅ ያልሆነውን ሀብት በማይመለስና በነጠታ መልኩ (endowment) ተረከበ በባለአደራነት ለማስተዳደር የተቋቋመ መንግሲታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። በዚህ መሰረት ንብረቱ ሆኖ በግለሰብ ሳም በቪር ኩባንያዎች መልኩ የተቋቋመው በስራ ላይ የነበሩ በኮንስትራክሽን፣ ቡትራንስፖርት፣ በማዕድን፣ በማኑፋክቸሪንግ መዘተ ዘርፎች ተሰማርተው ሲንቀሳቀሱ በነበሩ በርካታ ኩባንያዎች በስጠታና በማይመለስ መልኩ ተረከበ ሲያስተዳድር ቆይቷል። በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በተሬ ንንዘብ መልኩ ተቀማጭ የነበረ ሀብትንም ተረከበ ፋብሪካዎችን ለመገንባት ሲጠቀምበት ቆይቷል፣ በማለት ይገልጻል።

ስዩ ኤፈርት የተመሰረተበት አላማ የህዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍና የትግራይ ክልላዊ መስተዳደርን ለመደገፍ እንደሆነ በገፅ 337 ላይ፣

"ኤፈርት የተመሰረተበት አላማ ሚሊየነር ገለሰቦችን ለመፍጠር አልነበረም። አላማው በአንድ በኩል በስጠታና በትርፍ መልክ ወደፊት የገበየ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ደግሞ በአክሲዮን ሽያጭ የሚገኘውንና ሊገኝ የሚችለውን ንንዘብ መልሶ ኢንቨስት በማድረግ ቀጣይነት ያለው የልማት ሰራ ማካሔድ ሲሆን፣ በሌላ ደግሞ ከሚገኘው ገንዘብ የተወሰነ በጀት አየመደቡ በህዝባ ያሉትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመቅረፍ የነበሉ መንግስትን የልማት ሰራዎች መደገፍ ነበር" በማለት ይገልፃል።

ስዩ አብርሃ የኤፈርት ዋና ሰራ አስፈጻሚ በነበረ ሦስት ድርጅቱ ያስቀመጠውን ተልእኮ ለመፈጸም ጥረት ማድረጉን ያመለክታል። በአንድ በኩል በውጭ ባንኮች የተቀመጠ ንንዘብ ለስፔኩሌተሮች ትርፍ ማካበቻ ውሎ የነበረውን ወደ ትግራይ በማስገባት ፋብሪካዎች እንዲከፈቱ ማድረጉን ያስረዳል። በሌላ በኩል በትጥቅ ትግሉ ወቅት ሊጀቻቸውን፣ የቤት አባወራ እና እማወራዎቻቸውን ያጡትን ቤተሰቦች ለመደገም መቻሉን ይናገራል። ይሁን እንጂ እሱ ከህወሓትና

ኤፈርት ከተባረረ በኋላ ኤፈርት በሚሊዮኖች ቢያገበሳብስም አለማው መቅየሩን እንደሚከተለው ይገልፃል፣

"በአሁኑ መቅት ድርጅቱ ከሉንዚህ ቱብረካዎች በቀን በቀን በሚሊዮኖች ምኒቶመር ጀሚ ሊዮንፕ ነው። ይሁን እንጂ እኔ ከለቀቅሁ ወዲህ የጨመረ ቱብረካ የለም። ለህብረተሰቡ ማህበራዊና ሊኮኖሚያዊ ችግሮች መፍቻ ምሚደረግ አስተዋጽኦም የለም። ሁላችንም በሚዲያ እንደምንሰማው የትግራይ ከተሞች በዉሃ ጥም አየተቃጠሉ ናቸው። በሚሊዮኖች ምቆጠሩ ለሴት ምያንቀላቅለው ኤፈርት ትግራይን መልሶ ለማድጅም ተብሎ የተቋቋመው ድርጅት ግን እንዳችም ለርምጃ ለለመበደም በማለት ትዕምት አላማውን እንደሰተ ይገልጣል።

የኤፈርት ዋና ስራ አስፈፃሚ የነበረው ስዬ አብርሃ በዚህ ማቀም አልፈለጠም። የኤፈርትን በህጋዊ መንገድ በኢትዮጵያ ፍትሃ ብሔር ህግ መሠረት ፃተቋቋመ መሆኑን እንድናውቅለት ፈልጓል። የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብም ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንዳፀደቀ በገጽ 338 ላይ፣

"ከፍ ብዬ እንደጠቀምኩት ድርጅቱ (ኤፈርት) በሀገሪቱ ፍትሃብሔር ህግ መሠረት የመመስረቻ ጽሑፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ለሚመለከተው የክልሉ ጽ/ቤት አቅርቦ በዚሁ መሠረት የተመዘገበና አውቅና ያገኘ ድርጅት ነው። በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የድርጅቱ ምክር ቤት ነው" በማለት ለትዕምት ህጋዊ ሠውነት ይሠጣል።

አቶ ስዬ በመጨረሻ የገለጠው የኤፈርት የአመራር ስርአት ነው። የትዕምት የአመራር አርከን ከምክርቤት ጀምሮ፣ ቦርድ፣ ማኔጅመንት ኮሚቴ እና ዋና ስራ አስፈጻሚ ምሚባል እንደሆነ ያስረዳል። ቦርዱና የምክርቤት አባላቱቹ እነማን እንደሆኑና የት እንደሚሰበሰቡ በገጽ 338 ላይ፣

"በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የኤፈርት ምክርቤት ሠብሳቢ እቶ ተወልደ ወልደማሪያ ነበሩ። ከቦርዱ ቱጥሎ ያለው የአመራር አርከን የኤፈርት ማኔጅመንት ኮሚቴ ሲሆን እኔ በቦርድ እቅራቢነት በምክርቤት አጽዳቂነት የተመደብኩ የማኔጅመንት ኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ነበርኩ። የድርጅቱን ስራ በቋሚነት ለመስራት የተመደብነው ሰዎች የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የተባልነው ስንሆን፣ እኔን ጨምሮ በዚህ የተመደቡት እቶ ስብሃት ነጋ፣ አቶ አርከበ እቁባይ፣ እቶ ቴምድሮስ ሐጎስ፣ እቶ አባዲ ዘሙና እቶ ሙሉጌታ ገ/ህይወት ስንሆን ስድስታችንም የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ነበርን። ቦርዱ እቶ ተወልደ ወ/ማሪያም፣ እቶ አለምሰገድ ገ/አምላክና እቶ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሶስቲታችን የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላቱንም ያካተተ በዘጠኝ አባላት የተዋቀመ የድርጅት አካል ነበር። የቦርድ ስብሰባዎች የሚካሄዱት በጠቅላይ

ሚኒስትሩ ቢሮ ወይም በመኖሪያ ቤታቸው ሲሆን መደበኛና ልዩ ልዩ ሰብሰባዎች በማካሄድ ከማኔጅመንት ኮሚቴው የሚቀርቡትን ሪፖርት ይገመግማሉ፣ የሚቀርቡለትን የስራ አቅጅቶች ያፀድቃል ነበር" በማለት ይገልፃል።

እንግዲህ አቶ ስዩ አብርሃ ኤፈርትን በተመለከተ የገለጠው ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል። ኤፈርት በኢትዮጵያ ፍትሃብሔር ህግ መሠረት የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደሆነ አንዲሁም መቀሌ የተመዘገበ መሆኑን ነግሮናል። አቶ ስዩ "ነጻነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ" ብሎ በሠየመው መጽሀፉ የህገሪቷን አዋጆች አሠልቺ በሆነ መንገድ አንቀጽ በአንቀጽ በጠቀሰበት ሁኔታ ይህን ኤፈርት የተቋቋመበትን የፍትሃብሔር ህግ ከመጥቀስ ተቆጥቧል። ለምን ተቆጠበ የሚለውን ጥያቄ አንስቶ ጉዳዩን በዝርዝር መመርመር ያስፈልጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የምዝገባ ቦታውን ለምን መቀሌን መረጠ?... ምዝገባው መቀሌ እንዲካሄድ የፍትሃብሔር ህጉስ ይፈቅዳል ወይ፣ የሚለውን በድጋሚ መመልከት ከጀርባ ያለውን ፍላጎት ለማወቅ ያስችላል።

***

ጉብሩ ምን አለ?

የጎብሩ አስራት "ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለው መጽሁፍ ኤፈርት እንደተመሰረተ ከገጽ 200-202 ባለው ላይ የሚከተሉትን ቁምነገሮች ያስቀምጣል፣

"በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ከንግድ፣ ከእርዳታና ከጦር ምርኮ ያሰባሰብነው የተወሰነ ሀብት ስለነበር እንዴት ስራ ላይ ልናውለው እንችላለን የሚለው ጉዳይ በህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ እነጋጋሪ ሆኖ ነበር። ይህንን ገንዘብ ለተሰዉ ታጋይ ቤተሰብ በማከፋፈል ወይም ደግሞ በተደራጀ መንገድ ልማት ላይ ማዋል ይሻላል የሚሉ አማራጮች ቀርበው ውይይት ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ ገንዘብ ለልማትና የኢኮኖሚ ለውጥ ለማምጣት እንዲውል ተስማማን። ይህ ሲሆን ግን ገንዘቡ በአካባቢው የኢኮኖሚ ለውጥ በሚያስከትል መንገድ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ተብሎ አንድ የኢንቨስትመንት ተቋም እንዲመሰረት ተወሰነ። የዚህ ተቋም መመስረት ፋይዳ በአጭሩ የነበረውን ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ብቻ ሳይሆን የልማት ሀሳቦቻችንም ስራ ላይ ማዋልና ልማት ማረጋገጥ ነበር..." በማለት ይገልፃል።

አቶ ንብሩ ኤፈርት የተመሠረተው የፖለቲካ ፓርቲዎችን ህግ በሚያከብር ሁኔታ መሆኑ ይገልጣል። በዚህም ሳይወሰን የህግ ባለሙያዎቹ ባቀረቡላቸው ጥቆማ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት (የሚሆን መልኩ አንዳቋቋሙት ይናገራል። በተጨማሪም በበጎ አድራጎት ድርጅት ህግ አንደተዳነገው ኤፈርት የግብርና እና ማዕድን ላይ እንዲያተኩር መደረጉን በገጽ 201 ላይ፦

"በዚህ መሰረትም የትግራይ መልሶ ማቋቋሚያ ተቋም 'ትዕምት' የሚል ድርጅት ተቋቁመ። ፓርቲዎች በንግድ ስራ እንደማይሰማሩ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ያመለከት ስለነበር በኢትዮጵያ የተለየ አካሄድ አይኖርም በሚል የዚህ አይነቱ የልማት ተቋም ሊመሰረት የሚችልበትን ሕጋዊ ማእቀፍ ተነጋግረንበት ነበር። ይህን መሰል ተቋም የሚያስተናግድ የበጎ አድርጉት ድርጅት (foundation) ማቋቋሚያ ሕግ እንዳለ የሕግ ባለሙያዎች ጠቁመውን የበጎ አድራጎት ድርጅት አንዲሆን ተወሰነ። የበጎ አድራጉት ድርጅት ሀብት ለግለሰቦች አንደግይከፋፈልና ለልማት ሰራዎች ብቻ አንደሚውል ሕጉ ይደነግግ ነበር። በዚህ መንገድ የተቋቋመው ትዕምት አንዳንድ የልማት ሥራዎችን ለመጀመር የተናት አንቅሲቃሲ አድርጉ በመጀመሪያ የማዕድንና የግብርና ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት አድርጉ የሲምንቶ፣ የሰብነ በረድና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችን የማብርና ኩባንያ ሊያቋቁም ቻለ..." በማለት ይገልጻል።

ንብሩ አስራት ያስጨነቀው "ኤፈርት የማነው?" የሚለው ጥያቄ ነው። የህግ ሙያተኞቹ ባቀረቡላቸው ምክር መሠረት በጎ አድራጎት ያደረጉት ኤፈርት ባለቤቱ ማነው የሚለው ርግጥም አስጨንቆታል። በገጽ 202 ላይ ይህንን ቁጭቱን እንደሚከተለው ይገልፃል፦

"ትዕምት የማን ነው? ለሚለው ጥያቄ እስከ አሁን ድረስ መልስ አልተገኘለትም። በአርግጥ ከሕግ አንጻር ትዕምት የፓርቲ፣ የመንግስት ወይም የሕዝብ ሳይሆን በበጎ አድርጉት ስም የተቋቋመ ድርጅት እንደሆነ ታውጇል። ከሕግ አንጻር ይህን ይባል እንጂ አጠቃላይ እንቅስቃሴውን የሚመራውና የሚቆጣጠረው ግን ሕዝቡን አወከላለሁ፣ የከልሉን መንግስት እመራለሁ የሚለው ህወሓት ነው። በመሆኑም ህወሓት ፓርቲም፣ ሕዝብም፣ መንግስትም ስለሆንኩ የሁሉንም ጥቅም በሚያካትት ሁኔታ ሀብቱን እያሰተዳደርኩ ነው እያለ ነው። ያም ሆኖ የሁሉም ነው አየተባለ የማንም ሳይሆን ቀርቷል" በማለት ይገልፃል።

አቶ ንብሩ ለስራት የሚያስጨንቀው ሌላ ጉዳይ ኤፈርት ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚዘርፈው ሀብት ሳይሆን በኤፈርት ውስጥ የተንሰራፋው ብክነትና ዝርፊያ ነው። ትዕምት ውስጥ ያሉ አመራሮችና ሠራተኞች የሚያባክኑት እና የሚዘርቅት ተለይተው በህግ ተጠያቂ አለመሆናቸው አንደ እግር እሳት ይለበልበዋል። በተለይም ኤፈርት በፖሊሲ የሀገሪቷን ሲምንቶ በተቆጣጠረ

ውቀጥ ድርድሩ ውስጥ ያሉ የዋድሞ ታጋዮተ ወደ ሚሊኒየነርንተ ቢመነድጉ ግሃቱ ከምነው ብሂ አንደሚያሳክነው በገጽ 201 ላይ፣

"ትዕምት በቢሊዮኖች የሚገመት ካፒታል ባለቢት ቢሆንም፤ በበርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎች ቢሰማራም ሙያዊ ብቃት ያለውና በሰነ-ምግባር የታነፀ አመራር ባለመገኘቱ በተደጋጋሚ ለሊሳሬ፣ ለብክነትና ለዝርፊያ ተዳርጓል።... በትዕምት የባከነው7ና የተዘረፈውን ሀብት አስመልክቶ አስከ ዛሬ ድረስ ተጠያቂ የሆነ ግለሰብ የለም። ትዕምት ውስጥ ዝርፊያ አንደሚካሄደው በተሰየዩ መቅቶች በተደረጉ ግምገማዎች ይፋ ቢደረጉም በጥፋተኝነት የተገመገሙት ግለሰቦች አንጂም በሕግ አልተጠየቁም። አንዳንድ ትዕምት ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ግለሰቦች አጅግ ባለፀጋ አንዲሁም ሚሊየነሮች ሆነው ያለምንም ተጠያቂነት በአገሪቱ ሲኖሩ ይታያሉ። አንዳንዶቹም ከምንም ተነስተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ትላልቅና ብዙት ያላቸው መኪናች ማስማሪት ሲጀምሩ፣ የተወሰኑትም ከተጠያቂነት ለማምለጥ አገር ጥለው ጠፍተዋል። ሲሚንቶ ውድ በሆነበትና ምርቱን ሰርጭውን የትዕምት ድርጅቶች በተቆጣጠሩበት ወቅት አየር ባየር ንግድ ውስጥ በመግባት ከፍተኛ ሀብት ያካበቱት ወገኖችም ከትዕምት አመራር ዕይታ ውጭ ነበሩ ለማለት አይቻልም በማለት ይገልፃል።

አቶ ገብሩ አስራት ኢፈርትን በተመለከተ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተለይም በምርጫ 97 የተሳተፉትን አንደ "ቅንጅት" ያሉ ድርጅቶችን ወቅሷል። የወቀሳው ምንጭ ተቃዋሚዎች "የፖለቲካ ትርፍ" ለማግኘት የትግራይ ህዝብ ከኤፈርት ኩባንያዎች ተጠቃሚ ሆኗል ማለታቸው እንደሆነ ያስረዳል። የትግራይ ህዝብ ከእነዚህ ኩባንያዎች የተረፈው መሰረታዊ ጥቅም የለም በማለት በዘጽ 436 ላይ፣

"የትግራይ ህዝብ በተለየ ተጠቅሟል ለማለት አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ሲያራግቡትና ጊዜያዊ ትርፍ ለማግኘት ሲቀሰቀሱበት የነበረው ጉዳይ የኤፈርት ኩባንያዎች የትግራይን ህዝብ ጠቅመዋል የሚለው ነበር። ሆኖም የትግራይ ህዝብ ከእነዚህ የንግድ ኩባንያዎች ያተረፈው መሠረታዊ ጥቅም አልነበረው። ምክንያቱም ኩባንያዎቹ በህወሓት አመራር ቁጥጥር ስር ሆነው ለከፍተኛ ምዝበራና ለዘመድ አዝማድ መጠቀሚያ ተዳርገው ነበርና።... ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ትዕምት በትግራይ ህዝብ ስም የሚነግድ የጥቂቶች ሀብት አንጂ የትግራይ ህዝብ የሚያዝበትና ባለድርሻ የሆነበት ተጂም አንዳልሆነ ተቃዋሚዎቹ መግንዘብ ነበረባቸው። ተቃዋሚዎች ለፖለቲካ ትርፍ ሲሉ ገገርውን ፓርቲና ህዝቡን፣ ምርትና ግርዱን፣ አለመለየታቸው በርካታ የትግራይ ተመላጆች ዘንድ ሲጋትን ፈጥሮ ነበር" በማለት ያስገነዝባል።

አቶ ገብሩ አስራት ኤፈርት የትግራይ ህዝብን አልጠቀመም ብሎን ሲያበቃ በሌላ የመጽሐፉ ክፍል ላይ በትግራይ ህዝብ ዕይታ የትዕምት ድርጅቶች የትግራይ ህዝብ ተደርገው ይቆጠራሉ በማለት ይገልፃሉ። እናም ቅንጅት የኤፈርት ምርቶች ላይ ተአቅቦ እንዲደረግ ያቀረበው መመሪያ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ቡተለይም በጦር ሀይሉ፣ በፖሊሱና በደህንት ክፍሉ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች በቁጣ ተቃውሞት እንደነበር ያስረዳል።

ከሁሉም በላይ አስደንጋጭ የሆነው የአቶ ገብሩ ሀሳብ የኤፈርት ኢኮኖሚ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ያለው ደረጃ የገለጠበት ነው። በአቶ ገብሩ አምነት የትዕምት ምርት በህወሓት/ ኢህአዴግ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ኢምንት ነው። ይህም ለቅንጅት መሰረታዊ ስህተት እንደሆነ በገጽ 442 ላይ፡

"ቅንጅት የተሳሳተው በትዕምት በተመረቱ ምርቶች ላይ የተአቅቦ መመሪያ ሲያስተላልፍ ነው። ይህ መመሪያ ከሲቪል ዐድማ ጋር ተያይዞ እንደ ስልት ቢቀርብም ቅንጅት ከትግራይ ህዝብ ይበልጥ እንዲራራቅ አደረገው እንጂ የፖለቲካ ትርፍ አላስገኘም። በዚህ ረገድ የቅንጅት አመራር መሠረታዊ ስህተት ኢምንት የሆነው የትዕምት ምርት በሕወሓት/ኢህአዴግ ኢኮኖሚ ላይ ተጽእኖ ሲያሳድር ይችላል ብሎ መገመቱ ነው" ይለናል።

ገብሩ አስራት የትግራይ ህዝብ ኤፈርትን እንደራሱ ንብረት አድርጎ ይቆጥራል የሚልበት ክፍል ደግሞ በገጽ 442 ላይ፣

"ሁለተኛውን ይበልጥ ስህተት የሚለው ደግሞ በትግራይ ህዝብ ዕይታ የትዕምት ድርጅቶች አለመገንዘባቸው ነው። እንኳን በ1997 ዓ.ም. እና ከዚህም ቢሆን በርካታ የትግራይ ተወላጆች የትዕምትን ሀብት ሕዝቡ እንጂ የህወሓት አመራር እንደሰቡ የሚያገለበት መሆኑን አያውቅም። ይህን ለይነት አመለካከት ያለው ህዝብ የትዕምት ምርቶች አትግዙ ማለት በትግራይ ባለቤትነት የሚመረተውን ምርት አትግዙ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር። ይህም በትግራይ ህዝብ እንዲሁም በጦር ሀይሉ በፖሊሱና በደህንት ክፍሉ የነበሩትን የትግራይ ተወላጆች ያስቆጣ ነበር" በማለት በትግራይ ህዝብና ኤፈርት መካከል ያለውን መንፈሳዊ ቁርኝት ያስገነዝባል።

***

"የህወሓት ወለፈንዲዎች"

የአቶ መለስም ሆነ እንጂ ሆኗል ተበሎ የተባረረው የህወሓት ቡድን ቢፓርቲያቸው የኢኮኖሚያ የበላይነት መረጋገጥ ላይ ልዩነት ያላቸው አይደሉም። ሁሉም "ኢኮኖሚውን

በመቆጣጠር የበላይነት መያዝ ፖለቲካውን ለመቆጣጠርና የበላይነት ለመያዝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የሚለውን የአምባገነኖች ፍልስፍና ሳይ የጋራ እምነት አላቸው። ፓርቲው በቅንጅትም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢኮኖሚውን በመቆጣጠርና ነፃ ገበያውን ድምጥማጡን በመጥፋት የበላይነቱን በማረጋገጥ ዙሪያ "ህወሓታዊ" መግባባት ፈጥረዋል። በመሆኑም የኤፈርት መፈጠር ሞኖፖሊ ሊኖለበት መሰዳደር ትግሉ ያንንነው ግንዛቤ የት አናደርገው በሚል ታሪካዊ አጋጣሚ ሳይሆን ሆን ተብሎ በፖሊሲ ሠነድ ተደግፎ የተፈፀመ ነው። በፖሊሲ ሰነዱ በተቀመጡት ስትራቴጂካዊ ስልቶች ዙሪያ ደግሞ የመለስ ቡድንም ሆነ አገኟኩ በቂ ግንዛቤ የተንተባተሰ፤ ከራስ አልፎ ሌላውን የህወሓት አባል ሊንደከትራት ያይረጉ ናቸው።

በመሆኑም ህወሓትንና መሰረቱ ነው ብሎ የሚመራውን ሀገሀብ አማኖ ለሚከወጣትና በሌለው ሀብት ላይ ተመሰርቶ ከፍ ከፍ ለማድረግ የተሔደበት መንገድ የመለሰም ሆነ ሰአገኟት የተፈረጁት ታጋዮች የጋራ ፍላጎት ነው። ሌሎችን የብዝበዛና የጭቆና ኢላማ ያደረጉት በጋራ ውሳኔና በተመሳሳይ የህሊና ደረጃ ነው። ህወሓት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚሳወተው ሚና እንደ ፖሊቲካው ሁሉ ማንባር ቀደምና ተወዳዳሪ የሌለው እንዲሆን ያደረጉት በህብረት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የነፃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አንዳይኖር፤ የግሉ ከፍለ ኢኮኖሚ ወደዳር ቀጥሎ ከጨዋታ ውጪ እንዲሆን፣ ኤፈርት ወሳኝ በሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች ላይ ሞኖፖሊ በመፍጠር ሀገራዊ ከበርቴ እንዲሆን ያደረጉት ያለምንም ልዩነት ነው። አንዱ ከደሙ ንፁህ ሌላው ተጠያቂ የሚሆንበት አድል የለም። "ጠባብ ብሔርተኝነት" በሁሉም ዘንድ የነበረ እና ያለ ነው።

ያለፉት መንግስታት ትግራይን ነጥለው ገፍተዋል፣ አደህይተዋል፣ ኢንዱስትሪ አልባ አድርገዋል፣ ድሔውማናይዜሽን ፈፅመዋል፣ የትግራይን እንጡራ ሀብት በመዘረፍ ወደ መሐል ሀገር ወሰደዋል የሚለውን ቁጭት የሚፈጥር "ማኒፌስቶ" ያወጡት ቢጋራ ነው። እንዳንዶቹ ማኒፌስቶው ሰማውጣት ሂደት ባይኖሩበት እንኳን ሞፈርና ቀንበሩን ጥሎ ወደ በረሃ እንዲገባ የትግራይ ገበሬን የማሰኙት ስራ ሰርተዋል። አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ ያወጧቸው የተለያዩ ደክመንቶች ይህንን የሚያጠናክሩ ናቸው። "ከእነዚህም ውስጥ በመጋቢት 1984 ዓ.ም የተጻፈው "አብዮታዊ ዴምክራሲ በኤርትራና በአንድነት ጥያቄ" ላይ የሚለው መጽሐፍ፤ ከአንድ አመት በኋላ (በ1985 ዓ.ም) የተፃፈው "አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎቻችንና ቀጣይ ተግባሮቻችን" ለነደ ኤፈርት አንደ አዲስ ሲደራጅና አቶ ስዩ አብርሃ ከመከላከያ ሚኒስቴር ወደ ኩባንያው ሮ ስራአስፈፃሚነት ሊመደብ የወጣው "ኤፈርት ኢምፓወርመንት ፕላን እና ፍኖተ ካርታ" ሰነዶች ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው። ርግጥ አንቫ የተባለው ቡድን ከህወሓት ከተባረረ በኋላ

"ኢህዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮች" የሚሉ መፅሐፎች በማውጣት የበለጠ እንዲጠናከር ተደርጓል። የኢትዮጵያን ካፒታሊስት ስርአት የሚመራው ኤፈርት እንደሆነ ቢተመጥም ክሱሎች ደጋፊ ሀይሎች (ትልማ፣ ማረት፣ የትግራይ ወጣቶችና ሴቶች ማህበር) ጋር የሚኖራቸው ትስስር የበለጠ ዘርዘር ብሎ የተቀመጠው ዘግየት ብሎ ነው።(የዚህ ማሻሻያወሻ አላማ የኤፈርትን የውንብድና ካፒታሊስት የመገንባት ሂደት በመሆኑ ስለ ማህበራት (ትልማ፣ ማራት፣ ትግራይ ወጣትና ሴት ማህበራት) ማንሳት አልተፈለገም። የትልማ፣ ማራትና የመሳሰሉት ማህበራት ጉዞ እንደ አፈርቱ ሁሉ ራሱን የቻለ መድብል ይወጣዋል። የትልማ ማረትና የመሳሰሉት ማህበራት ታሪካዊ መነሻ፣ ፋይናንስ ምንጫቸው፣ ከኤፈርት ጋር ያላቸው ግኑኝነት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የጦዘውና የደህንነት መዋቅር ለመዘርጋት የሔዱበት ርቀት፣ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ የወከሉትን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት የሔዱበት መንገድ፣ ከህወሓት ጋር ያላቸው ትስስር... ራሱን በቻለ ማሻሻያወሻ ይመጣል።)

***

"ኢህዮታዊ ዴሞክራሲ በኤርትራና በእንድነት ጥያቄ ላይ"

ይህ ህወሓት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ከእንድ አመት በኋላ በመጋቢት ወር 1984 ዓ.ም የተፃፈ መጽሐፍ ዋነኛ ይዘቱ የኤፈርት ጉዳይ ቢሆንም ሌሎች ቁም ነገሮችንም ይዳስሳል። ከእነዚህ ቁም ነገሮች ውስጥ በገጽ 28 ላይ ህወሓት/ኢህአዴግ ደርግን ለመጣል ሲታገሉ ከነበሩ አማጺያን ልዩ የሚያደርገው ጠባይ እንዳለው የተገለጠበት ነው። ህወሓት እንደ ሕጎግ ካሉ ሌሎች ትጥቅ እንስተው ከሚታገሉ ነፃ አውጪዎች በተቃራኒ ያለምንም ማቅማማትና በጦርነት የማረከውን ወታደራዊ ያልሆኑ ንብረቶች ለመንግስት ማስረከቡን ያበሰረል። በሌላ በኩል ሌሎች ሃፍጥ እንግበው ደርግን ለመጣል የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙርኮ ያገኙትን ንብረት በሙሉ ወርሰዋል ይላል።እነሆ፣ ህወሓት የማረከውን በሙሉ ለመንግስት መልሷል የሚልበት አንቀጽ በገጽ 28 ላይ፣

"ማንኛውም የታጠቀ የተቃወሞ ሀይል አንድን አካባቢ ከደርግ ጋጽ አውጥቶ በሚቆጣጠርበት ጊዜ የሚያገኘውን የመንግስት ንብረት በምርኮ አንደያዘ ንብረት ቆጥሮ መውሰድ የተለመደ ነገር ነው። ይህ አሰራር የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት አባላት የሆኑ የታጠቁ ድርጅቶች ሁሉ በተግባር ሲተረጉሙት የነበረ አሰራር ነው። አሰከዛሬ በጦርነት የማረከውን ወታደራዊ ያልሆነ ንብረት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያስረከበና በማስረከብ ላይ ያለ ድርጅት ኢህአዴግ ብቻ

ነው። ሌሎች ድርጅቶች ምርኮዎቹ ይነስም ይብዛም ከደርግ የወሰዱትን መታደራዊ ያልሆነ ንብረት አሁንም እንደ ንብረታቸው ይጠቀሙበታል" በማለት ይገልጻል።

ይሑ ለነድ ሰህወሓት ይዘጋጅ አንጂ በኢህአዴግ ም/ቤት ለውይይት ቀርቦ እንዲፀድቅና የስራ መመሪያ እንዲሆን ተደርጓል። ህወሓት/ኢህአዴግ ወታደራዊ መሳሪያዎች ያልሆኑትን መንግስታዊ ንብረቶችን በሙሉ ለመንግስት አስረክቧል የሚለው አባባል በሙሉ ድምጅ የፀደቀ ነበር። በዚህ ውሳኔ ላይ የድርጅቱ ሊቀመንበር መለስም ሆነ ሰዬ አብረሃ ነበሩ። ተወልደ፣ ገብሩ አስራት፣ ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምአን፤ ኩማ ደመቅሳ _ ወዘተ ነበሩ። ሌሎች የነዉሐት ባለስልጣናት እና ሚኒስትሮችም በውሳኔው ላይ ተገኝተዋል።

ህወሓት ይሑን ይበል እንጂ በወቅቱ የነበረው እውነታ ከዚህ በተገላቢጦሽ ነው። ድርጅቱ ከትግራይ ጀምሮ መላው ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር በእጁ የገባውን የመንግስት ንብረት ጠቅሏል። ሰልጣን ከያዘ በኋላ ደግሞ ያንኑ መልሶ ለቀድሞ መንግስታዊ መሳሪያዎች ሲያከራይ እና ሲሸጥ ነበር። አራት ኪሎ ፓርላማ ፊትለፊት ያለው ሆንጻ ካለፈው መንግስት የተወረሰ ነው። ፌደሬሽን ምክቤት እና ፓርላማው ከኢህአዴግ ተከራይተው በየወሩ ከሃያ ሺህ ብር በላይ ሊፓርቲው ይከፍላሉ። የኤፈርት ንብረት የሆኑት ሬዲዮ ፋና፣ ዋልታ እና ሜጋ አምፊ ቲያትር የመንግስት ሀገኝ እና የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቭዥን ከምችዎችን በመውረስ ነው ስራቸውን የጀመሩት። አስከዛሬም ከኢቪኤ (ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎ) እና ኢቲቪ ለሚወሰዱት ዶከመንት አምስት ሳንቲም አይከፍሉም። ከዚህ በተቃራኒ ኢቲቪ ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ለሚላከለት መረጃ በየአመቱ ከፀሚሊዮን ብር በላይ ይከፍላል። ሩቅ ሳንሄድ በዚህ ማስታወሻ ላይ በየቦታው የተጠቀሱት መረጃዎች የሚያመላክቱት ህወሓት ለቁጥር አታካቹ የሆኑ የመንግስትና የህዝብ ንብረቶችን አየወረሰ፣ አንዳንዴም መልሶ አየከራየ የሔደ መሆኑን ነው።

አቶ መለስ የኤፈርትን አፈጣጠርና አሰራሊነት በዘረዘርበት ሰነዱ ምንም አይነት ውርስ እንዳልተካሔደ ይገልጣል። የኤፈርት ሀብት መሳሽና ዋነኛ ምንጮ ሰትጥቅ ትግሉ ለማካሔድ የሚያሰፈልጋቸውን ንብረት በማሰባሰቡ ምክንያት እንደሆነ ያስገነዝባል። ይህ ንብረትና ገንዘብ የእነዚህን ተቋሞች መነሻ ሆኖ እንዳገለገለ ያስረዳል። ከዚህም በተጨማሪ ኤፈርት በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተገኘ ገንዘብና ንብረት የተቋቋመ እንጂ ከመንግስት ያገኘው ወይም የወሲደው ቅንጣት ታክል ሳንቲም የሌለና ወደፊትም እንደማይኖር ይገልጻል። አቶ መለስ ይሑን ይበል እንጂ "ሱአላዊነት እና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ንብሩ አስራት የኤፈርት

የፋይናንስ ምንጭ ላይ "የጦር ምርኮ" የሚል ጨምሮበታል። ንብሩ አስራት የኤፈርት የፋይናንስ ምንጭ "ከንግድ፣ ከእርዳታና ከጦር ምርኮ የተሰባሰበ ሀብት" ብሎ የአይን ምስክርነቱን የሰጠው በነባር የህወሓት አመራሮች ያልተወደደለት ቢሆንም እውነታው ከዛ የራቀ አይደለም። እቶ ንብሩ በነከካ እጁ በጦር ምርኮ ከተሰባሰቡ ሀብቶች ዋና ዋናዎቹ ምን እንደሆነ ቢገልፀው የተሟላ ስዕል ይሰጥ ነበር። "ንብሩ የትግራይ ህዝብ ጠላት ሆኗል፣ ቅቤ የጠጣ ዱላ ለትግራይ ህዝብ ጠላቶች ሰጠ" በማለት የከሰሱት ነባር የህወሓት ታጋዮች እፍና እጃቸውን ይሰበስቡ ነበር።

ንብሩ አስራት በትግል ጓደኞቹ እንዳልተወደደለት ሁሉ ኤፈርትንና በትግራይ የሚገኙ ሌሎች አደረጃጀቶችን በጥልቀት ለሚከታተሉ ሰዎች ቅሬታ አሳድሯል። የቅሬታው ምንጭ የኤፈርት የፋይናንስ መሰረት ከንግድ፣ ከእርዳታና ከጦር ምርኮ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ምንጮችም መኖራቸውን እቶ ንብሩ በዝርዝር መግለፅ ነበረበት የሚል ነው። ከተለያዩ የኢትዮጵያ ከፍሎች ተነቅለው የተወሰዱ ጀነሬተሮች፣ ኤሌክትሪክ ፖሎች፣ የውሃ ጉድጓድ መቆፈሪያ ግዙፍ ማሽኖች፣ የሆስፒታል ቁሳቁሶች፣ የፋብሪካ ማሽኖች የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ የጭነት ማጓጓዣ ከባድ መኪናዎች፣ የአዲስ አበባ አውቶቡሶች_ መዘተ ገለጥለጥ አድርጎ ማሳየት እንደሚገባው ይናገራሉ። ይሔ ደግሞ ከህወሓት አባላት ውጭ በሚገኙ የኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ በሰፊው የሚነሳ መሆኑ ቅሬታውን ተገቢ ያደርገዋል። የኢህአዴግ ካድሬዎች ህገቡን በየአዳራሹ በሰበሰቡበን ቁጥር የምንጠየቃቸው በመሆኑ ዘወትር ምላሽ እጥተን የምንጨነቅበት ነው። እውነትም እርምጃው በአይን የሚታይ ቁሳዊ ነገሮች ላይ በመሆኑ ህዝቡን መዋሸት የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር አልተቻለም። ይህ የህዝብ ሰሜት ለረጅም አመታት የትግራይን ከልል በፐሬዝዳንትነት ለመራውና በአዲስ አበባ አስርተ አመታት ለከተመው ንብሩ አስራት የተደበቀ አይደለም። በተለይም ኤፈርት በተነሳ ቁጥር የአዲስ አበባ ህዝብ በንዴትና ቁጭት የሚገለጸው ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል አይደለም። ህወሓት በአንድ በኩል አዲስ አበባንና ህዝቧን ለመበቀል በሌላ በኩል ሀብቷን ለመዝረፍ የወሰዳቸው አርምጃዎች በእያንዳንዱ ነዋሪ ጭንቅላት ተቀርፀው የቀሩ ናቸው።በርካታ ምሳሌዎች ማንሳት ይቻላል።

በለማኔያዎቹ እጋማሽ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በሰፈው ሲነበቡ ከነበሩት የነፃ ፕሬስ ውጤቶች መካከል ጦቢያ እና አሌፍ የሚባሉ መጽሔቶች ይገኙበታል። ሁለቱ መጽሔቶች አንድ አስገራሚ ማስረጃ ከኢህአዴግ ቢሮ እና በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከነበረው ታምራት ላይኔ ቢሮ አፈትልኮ በመውጣት እጃቸው ይደርሰል። ጦቢያ በቁጥር ፣ ሚያዚያ 1985 ዓ.ም ላይ ጥአስራ አንድ ሚሊዮን ብር መይለኒት ከኢህአዴግ ተገዛ" በሚል ርዕስ አውጥቶታል።

ጉዳዩ እንዲህ ነበር፣

ህወሓቶች በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው የመደቡትን ታምራት ላይኔ እንደ ትንሣሄ ያስተላልፉሲታል። ትዕዛዙ ህወሓት የትግራይን፣ የወሎንና የጎንደርን አካባቢዎች በተቆጣጠረ ሰዓት ለህዝቡ መድሐኒት አድያለሁ አና ይከፈለኝ የሚል ነው። የተባሉትን ለመፈፀም የተነሳሙት ለታምራት ላይኔና ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር ለነበሩት ዶ/ር አዳነች ኪ/ማርያም በእስትኳይ ከፍያው እንዲፈፀም ደብዳቤ ይጽፉሉ። ዶ/ር አዳነች ድጋፍ ለማግኘት ኢህአዴግ ቢሮ ሲመጡ ቢሮውን የተቆጣጠሩት የህወሓት ኦባር ታጋዮች "የጨጮኑ አማራ ማዕከል ከሆነችው አዲስ አበባ በጀት እንዲቀነስ" ይነግሯቸዋል። ባገኙት ድጋፍ መሰረት የአዲስ አበባ ጤና ቢሮን ሲመለከቱ 6ሚሊዮን ብር ገደማ ይሆናል። ስለዚህ በመጀመሪያ ዙር ለህወሓት ይከፈለው ተብሎ ከተጠየቀው አራት ሚሊዮን ብር ይከፈለው ይላል። ስለዚህ ከአዲስ አበባ በጀት 65 በመቶ ተቀንሶ እንዲከፈል ትዕዛዝ ያስተላልፉሉ። አዲስ አበባ ለፀረ- ስድስትና ሌሎች ህከምናዎች፣ ለወሊድ አገልግሎት፣ ለተላላፊ በሽታዎች ክትባትና ቁጥጥር፣ ሊድንተኛ ተውሳክና ወረርሽኝ፣ ለሆስፒታል ሙያ መሳሪያዎች እና ሆስፒታልና ክሊኒክ ጥገና... ወዘተ ሁለት ሚሊዮን ብቻ ይበቃታል ተባለ። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ለታማሚ ቤተሰባቸው ጉልኮስ ከውጭ ገዝተው ካላመጡ ህከምናው እንደማይካሔድ ይነገራል።

ሁኔታው ያስገረማቸው የመጽሔት ባለቤቶች ተራ በተራ ዶ/ር አዳነች ኪ/ማርያምን "ይሔን ያህል በጀት ከአዲስ አበባ ሲዘዋወር አይጎዳችሁም ወይ፣ የአዲስ አበባ ህዝብ አይጎዳም ወይ? ተብለው ተጠየቁ። ከብርቷ አንድ ጊዜ "ይጎዳናል እንጂ! ለምን አይጎዳንም፣ ከ6ሚሊዮን ብር 4ሚሊዮን ብር በላይ ሲቀነስ በጣም ይጎዳል። ሰራችንንም ያደናቅፉል" የሚል ምላሽ ሰጡ። ደግሞ ሌላ ጊዜ "አበጀን"" ከፈለጋችሁ ልትከሱን ትችላላችሁ" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

የቃለመጠይቁ ከፊል እነሆ:-

ጥቢያ:- *ኢህአዴግ ትግራይን፣ ወሎንና ጎንደርን በተቆጣጠረ ሰዓት አወጣሁት ያለው 4269485.03 ከአዲስ አበባ በጀት እንዲቋረጥ ተወስኗል። ይህ በሰራችሁ ላይ ጉዳት አያስከትልም?*

ዶ/ር አዳነች:- *ችግር ማስከተሉማ እውነት ነው። በጣም ይጎዳል። ከ6ሚሊዮን ብር በጀት ከ4ሚሊዮን ብር በላይ ሲወሰድ ይጎዳል እንጂ! ለምን አይጎዳም?*

ጠቢያ፦ ኢህአዴግ ትግራይን ንጉርጉና ወሎን በተቆጣጠረ ጊዜ የሽምቅ ተዋጊ (ጎሬላ) አንጂ መንግስት አልነበረም። ማንኛውም ሽምቅ ተዋጊዎች መድሐኒት ወይም ሌላ ሌላ ነገር የሚያገኙት አንድም ከወጭ መንግስታትና ድርጅቶች በአርዳታ አለያም የመንግስት ግምጃ ቤት በመዝረፍ ነው። ስለዚህ የከፍያው ጉዳይ ሲነሳ አርሰውም ይህንን ጥያቄ አገናዝበዎት አንደሆነ ብዩ ነው?

ዶር/ አዳነች፦ በአጠቃላይ ሽምቅ ውጊያውን በተመለከተ አንዲህ ለማለት የረሳህ መሰት ነው። ኢህአዴግን በሚመለከተ ግን ይህን ላይነት ኢንፎርሜሽን የለኝም።

ጠቢያ፦ ኢህአዴግ ሶዲስ አበባን ከመቆጣጠሩ በፊት ላወጣው ቢጠይቅ አግባብ ነው ይላሉ?

ዶር አዳነች፦ የመንግስት አካል ከመሆኑ በፊት የማዕከላዊ መንግስት ባልደረስበትና አሱ በሚያስተዳድርበት ቦታ የተጠቀመባትን መድሃኒት አሁን አጠይቃለሁ ማለቱ ትከከል አይመስለኝም።

ጠቢያ፦ ወደ አራት ሚሊዮን አንመለስና ለምንድነው ንጉዘቡ ከአዲስ አበባ ጤና አጠባበቅ አንዲቆረጥ የተደረገው?

ዶር አዳነች፦ ከአዲስ አበባ በጀት ላይ ተቆርጦ ለኢህአዴግ አንዲሰጥ ያደረግነው ከገጠሩ በጀት ላለመንካት በማሰብ ነው። በአርግጥ የፓለቲካ ድርጅቱ (ኢህአዴግ) ንጉዘቡን መውሊድ የነበረበት መድሐኒቱን በሰጠበት አካባቢ በጀት ላይ እንጂ ዕዳውን ንጣባ ላይ ጭኖ አለያማም በማለት ነው።

ጠቢያ፦ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አሁንም መድሐኒት ከኢህአዴግ አየገዛ ነው?

ዶ/ር አዳነች፦ ባለፈው ዓመት ሊቶር ሚሊኮር (የኢትዮጵያ የመድሐኒቶና ኦጢኖ መገልገያ መሳሪያዎች ድርጅት) በአንድ በተሰየ የበጀት አጥረት በሰላ በከፍተ ደግሞ የወጭ ምንዛሪ ችግር ደርሶበት ነበር።

ድርጅቱ ከባድ የመድሐኒት አጥረት ስላጋጠመው ከሊሀአይግ በጽሁና በቅናሽ ዋጋ መድሐኒት ገዝቷል። ፖሚሊዮን ብር በሚጠጋ ግንዘብ። አንዲያውም መድሐኒቱን ሰጠን አንደምንክፍለ ኦግረናቸዋል። የወጭ ምንዛሪ ብናገኝማ ኖሮ መድሐኒቱን ከውጭ አናስመጣ ነበር።

እንግዲህ ከዚህ ቃሉመጠይቅ ብዙ ነገሮች መዞ ማውጣት ይቻላል። ቀደም ብሉ እንደተጠቀሰው ህወሓት፣ በወሎ፣ በሳንደርና በሊሎች አካባቢዎች በሽምቅ ተዋጊነት ቢንቀሳቀስ በአጁ የነበውን የመንግስት ንብረትና ቁሳቁስ በመውረስ መልሶ ይሸጠዋል። አሊያም የአርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለህዝቡ የሚሰጡትን መድሐኒት ጀና ሌሎች ህይወት አድን ቁሳቁሶች በመውረስ አንደነና መልሶ ለህዝቡ ይሸጣል። የመድሐኒት ሽያጩ የዚህ አካሔድ ግልፅ መገለጫ ነው። ህወሓት የሽምቅ ተዋጊ ሆኖ ሲያቢቃ ስልጣን በያዝ ማግለት የመድሐኒት ንጋዴ በመሆን ከመንግስት ካጠ ሚሊዮን ብር በላይ የጫካ ሒሳብ ሲያወራርድ ምንአልባትም በአለም የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲ ሳይሆን አይቀርም። ይህ አውነት ሆኖ ሲያቢቃ የመንግስትም ሆነ የአንጀው ቡድን በጋራ ተሰማምቶ ባወጣው ሰነድ ላይ "ወታደራዊ ያልሆነ ንብረት በሙሉ ለመንግስት መልስናል" ይሉናል። በመሆኑም የህወሓትና ኤፈርት የሁበት ሚስጥር ሲነሳ አቶ ገብሩ አስራት አንደገለጠው በጦር ሜዳ የተገኘ ንብረት ብቻ ሳይሆን የህዝብ ንብረት በመውረስና መፈለ በመሸጥ የተገኘ ነው። እነ አቶ መለስ "በጦርነት የማረከውን ወታደራዊ ያልሆነ ንብረት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያስረከበና በማስረከብ ላይ ያለ ድርጅት ኢህአዴግ ብቻ ነው" በማለት የሚናገሩት ምን ያህል መዋሸት እንደሚችሉ ያመላከተበት አጋጣሚ ነው።

***

የአቶ መለስ እና የአንጀው ቡድን ተቃርኖ ውስጥ ከከተቱት ጉዳዮች አንዱ የህወሓት ኩባንያዎችን ለይቶ መጥፋነ ወይንስ የኢህአዴግ ኩባንያዎች በማለት መግለጽ የሚለው ነው። አቶ መለስ ከመጀመሪያ አስከመጨረሻ ኤፈርት (ትዕምት) የሚል ቃል ሳይጠቀም "በተለምዶ የኢህአዴግ ኩባንያዎች" በማለት ለሁሉም "ኢህአዴግ!" የሚባለውን ሞኖፖብል ሊያሳጣቸው ፈልጓል። በመጽሀፉ ላይ ምሳሌ ወስዶ ሲያስረዳ አንኳን የኤፈርቱን መሰበ ሲምንዮ ፋብሪካ እና

ለህዴኑን ዳሸን ቢራ ፋብሪካ ነው። አቶ መለስ ኤፈርትን በስሙ የሚጠራውና የሚጽፈው ከህወሓት አባላትና የትግራይ ካድሬዎች ጋር ሲገናኝ ብቻ ነው። ከበረከት፣ አስጻለ፣ ግርማ ብሩና ለቦለማሪያም ጋር ሲሆን "የኢህአዴግ ድርጅቶች" ይላል።

ከአቶ መለስ በተሻለ ትዕምት፣ ጥራት፣ ዲንሾ፣ ወንዶ በማለት በአንድ ገጽ ላይ ለማጻፍ ያመረው ጉብሩ አስራት ነው። አንደ ጉብሩ እንላለጥ ከሆነ የህወሓት፣ ብአዴን፣ አህዴድና ደኢህዴግ ኩባንያዎች ልዩነታቸው የፋይናንስ አቅም ቢሆንም የተቀመጠላቸው ተልዕኮ ተመሳሳይ እንደሆነ ያስገነዝባል። ሁሉም ድርጅቶች በሀገሪቱ ስትራቴጂክ እገልግሎት የሚሠጡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ በመሰማራት ልማቱን የማፋጠን ግብ እንደተቀመጠላቸው ያብረዳል። ስትራቴጂክ እገልግሎት የሚባለውም ኮንስትራክሽን፣ ማዕድን፣ ትራንስፖርት፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ግብርና ፋይናይዜሽን... ወዘተ እንደሆነ ያመላክታል።

እርግጥ ነው ኤፈርት ህወሓት እንዳሰ ሁሉ ጥረት፣ ወንዶና ዲንሾ የሚባሉት ኩባንያዎች ብአዴን፣ አህዴድና ደኢህዴን ተጭቁሞላቸዋል። ጥረት ለብአዴን፣ ዲንሾ ለአህዴድ እና ወንዶ ለደኢህዴግ።

ጥረት በ20 አመታት ባደረገው እንቅስቃሴ አንድ የቢራ ፋብሪካ፣ አንድ የትራንስፖርት ድርጅት፣ አንድ ዮንግድ ድርጅትና አንድ የእርሻ ድርጅት ብቻ ማፍራት የቻለ ነው። በቅርብ ጊዜ ተመለከትኩትና የብአዴን ካድሬዎች በጠቅላላ እንደሚመለከሩት "ጥረት" የአራት የብአዴን ታጋይ ባለስልጣናት ቋሚ ንብረት ነው። እነዚህም በረከት ሰምአን፣ ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ)፣ ስሰሞን ሎዛና ካሳ ተክለብርሃን ናቸው። እነዚህ የብአዴን ታጋይ ባለስልጣናት "ቢኣማራነት" ጥያቄ ሚቀርብባቸው ባሻገር ራሳቸውን እንደ ህወሓት የሚቆጥሩና የአማራ ተወላጅ በሚባለው ህበረሰቡ ዘንድ እጅግ የሚጠሉ ናቸው። ይህንንም ራሳቸው ጠንቅቀው ያውቁታል። የብአዴን "ጡት አባት" የሆነው በረከት ሰምአን የአማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከገጠር ቀበሌ እስከ ማዕከላዊ ሚቴ ያሉት የብአዴን አባላት ሞቱን የሚመኙለት ናቸው። በካድሬነት ዘመኔም ሆነ በኋላ ኢህአዴግ አባላትና ህዝብ ዘንድ እንደ በረከት ሰምአን እጅግ የሚጠላ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። ብአዴን ከፍተኛ ካድሬዎች ውስጥ የፍትህ ሚኒስትር የነበረው ብርሃን ሃይሉና ሴኮቱሬ ጌታቸው ከምንም ጥርጥር በረከትን አቶ መለስ ሲጠራው 44 ሺማ ያበራሉ።

ግራም ነፈሰ ቀኝ በረከት "የብአዴኑ ስብሃት ነጋ" እንደሆነ ሁሉ ያጥረቱ የበላይ ጠባቂና አድራጊ ፈጣሪ ነው። ለኩባንያው ሰራ አስፈፃሚና አመራሮች የሚቃጥረውና የሚያባርረው አሳ ነው። ስለዚህም ይመስላል የኢህአዴግ/ብአዴን ካድሬዎች ሴኮቱሬ ጌታቸውና ፍሬህይወት አያሌው ጥረትን በስሙ ከመጥራት ይልቅ "ክረከት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ" በማለት የሚገልጹት። እንደፈለገ ቁሜ ብድግ የሚያደርጋቸውን ሰዎች በመመደብ የግሉ ኩባንያ አድርጎታል። ከበረከት ቁጥጥሮ የጥረት ባለቤት ሰለሞን ከበረ ነው። ይህ በረከት "ተነሳ" ሲለው የሚነሳ፤ ተቀመጥ ሲለው የሚቀመጥ ብዙዎች በከፋ አድርባይነት የሚከሱት ለው ጥረት ካሉት አራት ኩባንያዎቹ የምስቱ አክሲዮን ባለቤት ነው። አነዚህም ዳሸን ቢራ፣ ጥቁር አባይ ትራንስፖርትና ዘለቀ የአርሻ ልማት ናቸው።...

የጥረት ሦስተኛ ባለቤት ታደለ ካሳ (ጥንቅሹ) ነው። ጥንቅሹ ከበረከት ("ከብአዴኑ ስብሃት ነጋ") ጋር የአምቻ ጋብቻ ዝምድና ያለው ሲሆን እንደ በረከት ሁሉ በአማራ ህዝብ በከፍተኛ ወጪ የተጠላ ሰው ነው። ወደ አዲስ አበባ ተዘዋውሮ ሲመጣም የክልሉ ህዝብና የብአዴን ካድሬዎች "አይኑን አያሳዩን" በማለት በግልጽ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው። በዚህ ምክንያት በአማራው ህዝብ ላይ ቂምና ጥላቻ እንዲቋጥር አድርጎታል። ወትሮም ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ የህወሓት አባል የመሆን ፍላጎት እንዳለው በብአዴን አባላት የተገለጠ በመሆኑ፤ የትኛውም የብአዴን ካድሬ ጥንቅሹን እንደራሱ ጓድ ቁጥሮት አያውቅም። ህወሓት ለስለላ ያስቀመጠው ለው ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ጉበሩ አስራት "ዴሞክራሲና ሱአላዊነት በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሐፉ ተደሰ ጥንቁሹና ህላዌ የሴፍ ለህወሓት እጅግ ቅርብ እንደነበሩና እንደሚወደዱ አመላክቷል። እንግዲህ ጥረትን በዋና ስራ አስፈፃሚነት የሚመራው ሰው በአማራ ህዝብና በብአዴን ካድሬዎች የተባረረው፤ ህወሓት እንደራሱ ሰው የሚወሰደው ታደለ ካሳ (ጥንቅሹ) እንደሆነ ሲገለጽ የጥረትን ተልዕኮ በግልጽ ያመላክታል።

ኦርግጥ ከምርጫ ፵፯ በኋላ በአማራ ክልል በተከፈቱ የአባላት እና የህዝብ መድረኮች ኤፈርት እና ጥረትን በማውዳደር ህዝቡ እነ አዲሱ ለገሰን ተሳልቆባቸው ነበር። "ጥረት በየቤታቸው ቴሌቭዥን መስኮት ከዳሸን ቢራ ማስታወቂያ ከማለደመጥ ውጭ ምን ያደረገልን ነገር አለ?" በማለት አንገታቸውን አስደፍቶታል። የህዝቡ ቁጣ ለኤፈርትም አደገኛ እንደሆነ የተገነዘበው የህወሓት አመራር የተወሰኑ ድርጅቶችን በተጨማሪነት እንዲከፍቱ ፈቅዶላቸዋል። ከዚህ ፍቃድ በመነሳት ለዳሸን ቢራ ግብአት የሚሆን የብቅል ማምረቻ ፋብሪካ፤ በወሎ ከፍለሀገር የማር

ማቀነባበሪያ እና በመተማ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካን በመጎብኘት ላይ ጥቅሙ የተሰቆ አንጀራ ነው። በእነ ሦንቅሹ አፍ የሚነገር ተስቅሎ የተጣመጠ አንጀራ።

ከብአዴን "ጥረት" ቃኮሎ የምናገኘው ያለርሞ ህወሓቶ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሁሉንም ንብረት የሆነው "ዲንሾ" ነው። መቼም ስለ "ዲንሾ" መግለጽ በጣም ያስጨራል። እንደ እነድ ጊዜያቶች ተሳትፌያለሁ። ታዲያ በእራቱም ጉባኤዎች ተሳታፊ የሆኑ ኪድሬዎች ዲንሾን በተመለከተ ጥያቄ ያነሳሉ። በኋላ ላይ ከኢህአዴግ ቢሮ የተለየ ውሳኔ እንዲወሰን ተደረገ። "ኤፈርትም ሆነ አይቻልም" የሚል ውሳኔ ነበር። የነቀምቴንና የሸሸመኔውን የአህጉድ ጉባኤ በምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣን የመራው አምባሳደር ግርማ ብሩ የኢህአዴግን ውሳኔ አና የፖለቲካ ፓርቲዎቹ አቋድ በማብራራት የጉባኤተኛውን አፍ አዘግቷል። አምባሳደር ግርማ በምሁራዊ አንደበቱ "የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህግ በግልጽ አንዳስቀመጠው የፖለቲካ ፓርቲዎች የንግድና ኢንቨስትመንት ኩባንያዎች አይኖራቸውም። አህጉድ/ኢህአዴግ ደግሞ ከማንም የፖለቲካ ፓርቲ በላይ ሀገን የማከበር ግዴታ ስላለበት ምንም አይነት ኩባንያዎች አንዳይኖሩት አድርጓል። በመሆኑም የድርጅታችን ንብረት ባልሆነ አና ህጉ በማይፈቅድልን ጉዳይ ላይ በጉባኤ አንሰቶ መጋገር አይቻልም በማለት አሰረድቷል። ጉባኤተኛው አያጉረመረመ ቢሆን በግልኮሜንት ተቃውሞ በመድረክ ላይ ከማንሳት ተቆጥቧል። የጉባኤው ፕሬዝዲየም አባጁለ ጉዳ ጉባኤተኛው ሲጠይቅም፣ ግርማ ብሩ ሲመልስም፣ ጉባኤተኛው ሲያጉረመርምም ከት አያለ ይስቅ ነበር። ምስት ጊዜ! ታድሎ!!

የሆነው ሆኖ ዲንሾ ሲያሜውን "የተምላ ኢንዶውመንት የኦሮሚያ ልማት በማለት ከመቀየር ውጭ አንዳችም የገነባው ፋብሪካ፣ ኢንዱስትሪ፣ ኮንስትራክሽን፣ ማዕድን ልማት_ ወዘተ የለም። "በቱጥር አራት በግብር አንድ" የሆኑት የዲንሾ ኩባንያዎች በሀገር ውስጥ ሚት ይነግዳሉ። ከውጭ ሀገር ደግሞ የቻይና ጫማ፣ የቻይና ላስቲክ ምንጣፍ፣ የቻይና አርሳስ፣ እስኪርቢቶ እና ደብተር በማስመጣት በጅምላና ችርቻሮ ይነግዳሉ። አርግጥ ነው ዲንሾ አማልጮችንድን ከማዳበሪያ ገቢያ ለማውጣት በተሰጠው መመሪያ መሰረት ተልዕኮውን ቢፈጽምም መጨረሻ ላይ በ30 ሚሊዮን ብር ኪሳራና የባንክ እዳ ከጨዋታ ውጭ ወጥቷል።

በሣርማ ብሩ እና ኩማ ደመቅሳ የበላይ ጠባቂነት ሲመራ የነበርው የዲንሾ ቦንሜድ ስራ የሌብነት፣ የዘመድ አዝማዲና ያጥቅም ትሥሥር መፈ ተሞሃያን ነበር። በኦሮሚያ ከልል ህገ-ወጥ ተግባር በመፈፀምም የሚታወቅ ነው። በ1996 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ በኩማ ደመቅሳ የታዝዙ የመከላከያ እና የክልሉ ልዩ ሀይሎች ሜት የሚልኩ ኑጋዴዎችን አፍኖ በመውሰድና በማሰር ቋታቸውን አንዲወረስ አድርገዋል። የተወረሰውን ሜት ዲንሾ ተረክቦ ሸጦታል። በኩማ እና ሣርማ አትወርክ ውሰጥ የተሰባሰቡ የድርጅቱ አባላት በሚሊዮን የሚገመተውን ገንዘብ ተካፍለዋል።

ውሃ-ቅዳ ውሃ-ሙልሰ የሆነው ዲንሾ በሚሰራው ስራ ኪሳራን ከመከናነብ ውጪ ለኦሮሞ ህዝብ ያስገኘው አንዳችም ጥቅም የለም። ቀደም ብሎ አንደተጠቀሰው "የኦሮሞ ዋርካ" የሆነውን ገብረየስ ቢሾ ከማዳበሪያ ንግድ ሰማስወጣት ከህወሓት ትዕዛዝ የደረሳቸው እነ ሣርማ ብሩ ለዲንሾ 100 ሚሊዮን ብር የባንክ ብድር ያለምንም መያገፐ እንዲፈቀድላቸው ይደረጋል። አምባሳደር ሣርማ የዲንሾ ንግድ ድርጅትን በመወከል ከውጭ ሀገር ከማዳበሪያ አምራቾች ጋር ድርድር ይጀምራሉ። ማዳቧሪያው ተሸምቶ ወደ አገርቤት ይመጣል። ምንም አይነት የማከሉሪያ ቻናል ሳልተከፈት የአመራርና ሰራተኛ ሰልጠና ሳልተሰጠበት፣ ቁጥጥር በሌለበትና የጠነረየሰ ቤኛ የማፍ አንባ ታክሰበት በ100 ሚሊዮን ብር የተገዛው ማዳበሪያ ድምጥማጡ ጠፋ። ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ የባንክ እዳ አይኖቹን እፍጥ መጣ። ዲንሾ የህወሓት አይደለምና እዳው አንደማይሰረዝና የተባለሸ አካውንት ውሰጥ አንደማይገባ በግልጽ ተነገረው። ሜቱን እየሸጠ አንዲከፍል ተወሰነበት። ወደ ጅቡቲ ሜት የሚልከበት ኮሪደር ተፈቀደለት።

በነገራችን ላይ ዲንሾ በንግድ ስራ ተሰማርቷል ሲባል ድርጅቱ በፈለገውና ትርፍ ያስገኝልኛል ብሎ በሚያስበው ሁሉ መሰማራት አይቻልም። "የቱምሳ ኢንዶውመንት ለኦሮሚያ ልማት" በማለት ስያሜውን ቢያሻሽልም ኦሮሚያ ያፈራቻቸውን አንደ ቡና ያሉ ምርቶችን ወደ ውጪ አንዲልክ አልተፈቀደለትም። አርግጥ ወደ ውጭ ቡና የሚልኩት አንደ ጉና ያሉ ኩባንያዎች የገበሬውን ቋንቋ መናገር ስለማይችሉ አርጥቡን ቡና ከገበሬው ገዝቶ ለእነሱ የማስክረቡን ስራ ተምሳ ይፈጽማል። የዶላሩን ትርፍ ጉና ይወሰዳል። ነገርን ነገር ያነሳዋልና ከጉና የቡና ንግድ ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት በኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት የተፈፀመውን አልረሳውም።
አንዲህ ነበር የሆነው፦

ጥቅምት 15 ቀን 2001 ዓ.ም ሙሉጌታ ብርሃኔ የሚባለው የጉና ሰራ አስኪያጅ ካፒታል ለሚባለው ጋዜጣ መግለጫ ይሰጣል። በመግለጫው ጉና ትሬዲንግ በሀገር ውሰጥ ካሉት ቡና ላኪዎች ትልቁ እንደሆነ አስታውቋል። የካፒታል ጋዜጣን ዜና ተከትሎ ብሉንበርግ የሚባለው

የውጭ ዜና ወኪል አቶ ቡልቻ ደመቅሳን፣ አቶ ሁሴን አርዳውን (የቡና ላኪዎች ፕሬዝዳንትና ምላሽ መስጠት ያልፈለጉ)፣ አቶ እየሱስ ወርቅ ዛፉ (የንግድ ምክርቤት ፕሬዝዳንት)፣ እና በረከት ስምኦንን አነጋግሮ ነበር። በጥቅምት 20 የወጣውን የብሉንበርግ ዜና ሞኒተሪንግ በምናደርግበት ሰአት በረከት ከመጠን በላይ ተናደደ። "እኔ ስለ አዜብ ያልተናገርኩትን ከየት አምጥቶ ጨመረው? በአስቸኳይ ይጠራና ዜናውን ያንሳ" በማለት ደነፋ። ሞኒተሪንጉን ሰንጪርስ የፈረደብን እኔ እና ሽመልስ የብሉምበርግ ጋዜጠኛውን ጠርተን እንድናስፈራራው ተስማማን። የፓርቲ ኩባንያዎች ብሎ መጥራቱ ፍቃዱን እንደሚያስነጥቀው እንደንሣረው ተወሰነ። የብሉምበርግ ዜና በከፊል ይሔን ይላል፣

"Guna Trading House PLC, **owned by Ethiopia's ruling** par y, said it plans to become one of the nation's **biggest coffee exporters**, raising concern among industry observers that private industry may get crowded out...

The company began shipping the beans in July and aims to export at least 12,000 metric tons of coffee in the year through Jun, Mulualeme Berhane, general manager of Guna, said in an interview on Oct 22 in the capital, Addis Abeba "we are intending to export to Europe, the U.S.A and China," he said, adding that Guna is among at least four other Companies owned by the state or prime minister Meles Zenawi's ruling party intend to expand in the industry.

"There is no crowding out of private business by anybody," said Bereket Simon, Ethiopia's communication Minister, in an Oct 23 phone interview "This is a country increasingly becoming ruled by competition, by efficiency and price. I think the first lady will not be guilded by rent- seeking practices."

ሚዲያ ሞኒተሪንጉን እየሰራን ነፎ ስልክ ደወለች። በነፎ ስልክ የሚደውለው እቶ መለሰ ብቻ እንደሆነ ስለምናውቅ ድምጻችንን አጠፋን። በረከት በፍጥነት እንስቶ በተለመደው የትግርኛ ቋንቋ ማውራት ጀመረ። ሞኒተሪንግ የሠራንበትን ወረቀት እንስቶ በትግርኛ እየተረጎመ እነበበልት። የሰልክ ንግግራቸው አላልቅ ሲል አኔና ሽመልስ ተያይዘን ወደ አፔ ቢሮ ሔድን። ፀገኔት ለምትባለው ፀሀፊያችን የብሉንበርግ ጋዜጠኛ በእስቸኳይ እንዲመጣ መልዕክት እንድትነግረው አደረግን። እዛው በቆምንበት ደውላ ሊጋዜጠኛው ነገረችው። ሁሉንም ነገር ትቶ በእስቸኳይ እንደሚመጣ ነገራት። በነገራችን ላይ የውጭ ጋዜጠኞች ትፈለጋላችሁ ከተባሉ ካሉበት ቦታ ኮንትራት ታክሲ ይዘው ይመጣሉ። አዲስ አበባ ለእነሱ አድጉት ናት። አስረው የሚሙቱባት።

ኧና መቀመጫችን ላይ እንደተቀመጥን ኢንተርኮሙ ደወለ። ድምጽን ከፍ አድርጌ ተሜንኩት። በረከት ስምአን ነበር። ጊዜ ሳያጠፉ "ያንን ነጫጭባ ጋዜጠኛ ጠራችሁት ወይ" በማለት ጠየቀኝ። ፀሀፊው ደውላለት እየመጣ እንደሆነ ነገርኩት።

በረከት ቢድጋሚ አበደ።

"በደንብ ተነጋግረን ላንጨርስ እንዴት ትጠሩታላችሁ?_ አሁኑኑ ደውሉና ለፐሬስ ኮንፍረንስ እንደሆነና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሰረዙን ንገሩት። አሁን ላስበው ማናገሩ አስፈላጊ አይደለም። ዴሞክራቲክ ኢንስትሩመንት ተጠቅመን ሌላ ጊዜ እንቀጣዋለን" በማለት ትዕዛዝ ሰጠን። ፀገኔት ደውላ ነገረቸው ።

ወደቀደመው ጉዳያችን ስንመለስ የአሮሞን ልማት አፋጥናለሁ በማለት በበጎ አድራጎት ድርጅትነት የተቋቋመው ነጋዴው ዲንሾ የዝርፊያ ማዕከል በመሆን የአህዴድ ባለስልጣናትን አበልጽጓል። እቶ ሽፈራው ጃርሶ፣ ግርማ ብሩና ኩማ ደመቅሳ ከሜት ንግድና ሌሎች የዲንሾ ህጉ ውጮ እንቅስቃሴዎች ጋር አጅ ከፍንጅ ተይዘው ከስ ሊመሰረትባቸው ሲል በእቶ መለስ ቀጭን ትዕዛዝ እንዲቁር ተደርጓል። ይህን ለማወቅ በኢህአዴግ ቢሮ የሚሰራ አንድ ተራ ሰራተኛ መጠየቅ በቂ ነው። አሊያም የደብረዘይት የአህዴድ ካድሬ ዲንሾ አጥሮ ይዞት ከነበረው 30 ሔክታር የጣሊያን መድሐኒት አምራች እንዴት እንደወሰዱት ጠጋ ብሎ መጠየቅ ይቻላል።

ከአህዴድ "ዲንሾ (ቱምሳ)" የንግድ ድርጅት ቀጥሎ በአራተኛ ደረጃ የምናገኘው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ደኢሕዴግ) የንግድ ድርጅት የሆነው "ወንድ" ነው።

"ወንዶ" ጉና ስላልተወሊዶ በበጎም ሆነ በክፉ የሚነሳበት ነገር የለም። "ወንዶን ወንድ እደርገዋለሁ!" በማለት ዝቶ ዋና ስራ አስኪያጅ እንዲሆን ተደርጎ የነበረው ሚኒስትር መኩሪያ ሐይሌ የተሳካለት አይመስልም። ቢሆንም ራሱን የስልጣንና የህዝቡት ጋራ ላይ በመስቀል "ከወንዶች ጎራ" ተቀላቅሏል። "መኩሪያ ወንድ ነው!"

ምዕራፍ 14

"ምንስ አገባንና! ..."

"...የራሳቸው ሀጋዊ ሰውነት ያላቸው፤ መንግሲታዊ ያልሆኑ በጎ ኢድራጎት ድርጅቶች (ኢንዶውመንት) ናቸው።"

አቶ መለስ ዜናዊ

"የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮችና ስትራቴጂዎች"

"... ኤፈርት የመጭ አዲት አየተደረገ ለመንግስት ያቀርባል። ለፍትሕ ሚኒሴቴርም ሪፖርት ያቀርባል።"

አቦይ ስብሃት ነጋ (ቪኦኤ ሰኔ/2001/ ዓ. ም)

"ኢንዶውመንት በሚል የተመዘገበ ሀገር በቀል ድርጅት አንድ ብቻ ነው። "አስራት ማህው መታሰቢያ የሚባል ደብረብርሃን የሚገኝ ድርጅት ነው።"

አቶ ጌታቸው ሳንሩ

(በፍትህ ሚኒሰቴር የማህበራት ምዝገባ ዳይሬክተር ሪፖርተር

የካቲት 21 ቀን 1996 ዓ.ም)

***

ይህ ምዕራፍ የኤፈርት ህጋዊነት የሚመረመርበት ነው። የኤፈርትን ህጋዊነት ለንመረምር ደግሞ የተለያዩ ጥያቄዎች ማንሳት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በመጀመሪያ መፈተሽ ያለበት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ኤፈርት የሚባል በጎ ኢድራጎት ድርጅት ተመዝግቧል ወይ? ...መዝጋቢው ማነው? ...የት እና መቼ ተመዘገበ? ...የሚለው ይሆናል። በመቀጠል ትዕምት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በበጎ ኢድራጎት ድርጅትንት ተመዝግቧል የሚል እሳቤ ተወሰዶ ሕጉ በሚፈቅደው የስራ ስምሪት ላይ ብቻ ይሳተፍ ነበረ ወይ? የሚለውን መመለስ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ትዕምት የተጠቀመበት የገቢ ማስገኛ ዘዴ ሆኑ የሚፈቅድለትን ነበረ ወይ? የሚለውን ለያይዘ መቃኘት ያስፈልጋል።

ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትም ሆነ ሌሎች ውስጥ ለቁጥቻ ዘንድ የሚገኘውን መረጃ መፈተሽ አስፈላጊ ይሆናል። አንደ አድል ሆኖ የዘውትር ተባባሪዬ ሪፓርተር ትዕምት ከተመሰረተ 7 አመት፤ ህዉሓት ከተሰነጠቀ አራት አመት በኋላ ጉዳዩ በቅጥታ የሚመለከተው የመንግስት ባለስልጣን የቆይታ አንግዳ አድርጉ አውነቱን አንዲናገር አድርጐታል።

ጋዜጣው በየካቲት 21 ቀን 1996 ዓም. ቆይታ አምዱ አንግዳ አቶ ጌታቸው ጉንሱ የሚባል ባለስልጣን ነበር። ባለስልጣኑ *በፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ዳሬክተር* ነው። በትምህርት ደረጃው በሩሲያ ፒተስበርግ ዩኒቨርስቲ በሆግ የማስትሬት ዲግሪ አለው። በስራው መስክ በፍትህ ሚኒስቴር በዐቃቤ ሆግ ባለሙያነት ከስምንት አመት በላይ አገልግሏል። ከ1994 ዓም በኋላ በፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ጽ/ ቤት ኃላፊ በመሆን አገልግሏል።

ሪፓርተር ጋዜጣ አንደ አብይ ርእስ የተጠቀመበት አርፍተ ነገር **"ኢንደውመንት በሚል የተመዘገበ አንድ ሀገር በቀል ድርጅት ብቻ ነው"** የሚል ነበር። ይሄ ሀገር በቀል ድርጅት ማነውን አፈርት ነወይ?_ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ አንደሚከተለው ቀርቧል።

የመጀመሪያው የሪፓርተር ጥያቄ የፍትሕ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ጽ/ ቤት ስልጣንና ሀላፊነት ምን እንደሆነ እና ምን አይነት ማህበራትን አንደሚመዘግብ ለማሳየት የቀረበ ነበር። አቶ ጌታቸው ይህን የመጀመሪያ ጥያቄ አንደሚከተለው ምላሽ ሠጥቶበታል፣

"የፍትህ ሚኒስቴር ማህበራት ምዝገባ ጽ/ ቤት በፌደራል ደረጃ መመዝገብ ያለባቸውን ማህበራት በሙሉ ይመዘግባል። የሙያ፣ የህይማኖት፣ የልማት ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑና **አንቅስቃሴያቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑትን የመመዝገብ በሕግ ስልጣን ተሰጥቶታል።** _ሕጉ በ1952 አ•ም• የወጣ ነው። ሕጉን ተላልፈው በሚገኙ ማህበራትም ላይ እስከ መሰረዝ የሚደርስ ስልጣን በፍትህሀሌር ሀግ (ስአንቀጽ 404 ጀምሮ) ተሰጥቶታል። በማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/1959 ላይም የተደነገገ ነው _ለምዝገባ ሲቀርቡ የሚጠየቁት ሕጉ ላይ ያለውን ነገር ነው።

ግህበሩ መተዳደሪያ ደንቡን እንዲያቀርብና አምስት መሰራች አባላት እንዲፈርሙበት ሕጉ ያዛል። ከዚያ በኋላ ቅድ እንዲሞሉ እናደርጋለን። ሙሉ ኢድራሻ እንዲያስመዘግቡ እንጠይቃለን።" ይላሉ።

ሁለተኛው ትኩረት የሚሰጠው የሪፓርተር ጋዜጣ ጥያቄ የሚከተለው ነበር፤

"ቀደም ሲል እንደገለጹት ፅ/ ቤቱ የሚተዳደርበት ህግ በ1952 የወጣ ነው። ይህ ደግሞ በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ የማህበራትን መደራጀት የሚያበረታታ ሳይሆን የሚያዳክም፣ ወይም መንፈሱ በቁጥጥር ላይ ያተኮረ ነበር። ሕጉ አሁን ካለው የመደራጀት ህገ መንግሥታዊ መብት ጋር ሊይጋጭ/ም?" የሚል ነበር።

ለዚህ ጥያቄ አቶ ጌታቸው የሚከተለውን ምላሽ ሠጥቷል፤

"ህጉን በተመለከተ በዚያን ወቅት እንደዚህ አስቦ ሕግ ማርቀቅ ማለት በግሌ የማደንቀው ነው። እኛ አሁን እያረቀቅን ያለነው አዋጅ በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ከዚህ ዮተሻለ አይደለም። አማርኛ የማለተካከል ነገር ነው። ያኔ የወጣው ሕግ የነጠረ ሕግ ነው። የመቆጣጠር እዝማሚያ ያለው ከማን ሕግ ጋር ተጎጻጽሮ ነው? በሰለጠነውም፤ ባልሰለጠነውም አለም መንግስት የቁጥጥር ሰርአት አለው። ያንን የሚያገኘው ከሕግና ከደንብ ከተሰጠው ስልጣን ነው። እኔ አሁን ያለው ህግ ይሄን ያህል የሚያሰጋ ነው አልልም። በርግጥ በዛን ወቅት የማይታሰቡ ወቅቱና ዘመኑ የወለዳቸው ነገሮች ስላሉ ያንን በማሻሻያው ማከል ይቻላል። ከዚያ ውጪ ግን ሕጉ አያሰራም፤ አያንቀሳቅስም ማለት ምኑ ላይ ነው? ግልፅ አኮ ነው። በነገራችን ላይ አሁንም እየተረቀቀ ያለው የማሕበራት ህግ የምዝገባ ሰርአት ያው ነው። ...በእርግጥ አዲሱ የማህበራት ማሻሻያ ህግ ዘግይቷል። ዶሉ መጠናቀቅ እንዳለበት አምናለሁ።"

ይህን የባለስልጣኑን ምላሽ ተከትሎ ሪፓርተር፤

"እናም በ1952 የወጣው ሕግ ያሰራል፣ ችግር የለበትም ነው የሚሉን?" የሚል ጥያቄ ያነሳል።

ለቶ ጌታቸው በበኩሉ፤

"በወቅቱ የሚያሰራ ሕግ ነበር። አሁን አንዲት አንቀጽ ናት አላሰራ ያሉችን። ይኸውም የገቢ ማስገኛ የምትከለከለዋ አንቀጽ ናት። ሁልጊዜም ተለምኖ አይቻልምና የገቢ ማስገኛ /income generation/ መፈቀድ አለበት ነው። ...ከሚመለከተው አካል የንግድ ፍቃድ ወስዶ ለትርፍ

የሚሰራ ነጋዴ አለ። ይህ ጎበረተሰብ መያዶች ለትርፍ ይሰሩ ነበባል እንደሚጉጫጫ አርግጠኛ ነኝ" የሚል ምላሽ ይሰጣል።

ከዚህ ምላሽ መረዳት የምንችለው በኢትዮጵያ ፍትሃብሄር ህግ መሰረት የሚቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትርፍ የሚያመጣ ገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ መሰማራት የማይችሉ መሆናቸውን ይሆናል።

***

እነዚህ እንደመንደርደሪያ ከላይ የቀረቡ ጥያቄዎች እንደ ውሀ እያሰላቹ ወደ ዋናው ጉዳይ ያስገቡናል። አናም ሪፓርተር ጋዜጣ እንዲህ በማለት ጠየቀ፣

"በ1953 በወጣው ሕግ መሰረት ሊንደውመንት በመባል የሚታወቁ ድርጅቶች እንዲመዘገቡ ያዛል። በዚህ መሰረት ሊንደውመንት የሚባሉት ድርጅቶች ምዝገባ እካሄዱቸኒ?" የሚል ጥያቄ ያነሳል።

የጽ/ ቤት ሀላፊው አቶ ጌታቸው ጎንሱ እንዲህ የሚል ምላሽ ይሰጣል፣

"ሊንደውመንትን በተመለከተ እኛ ጋር የተመዘገበ እንድ ሀገር በቀል ድርጅት ብቻ ነው። እስራት ግዘው መታሰቢያ የሚባል ደብረብርሀን የሚገኝ ድርጅት መሆኑን እውቃለሁ። በአጠቃላይ በዚህ ረገድ ሁለት እይነት አደረጃጀት ነው ያለው። አንዱ የሰዎች ስብስብ ሲሆን ሌላው ደግሞ የማቴሪያል / ገንዘብ/ ስብስብ ነው። ሊንደውመንት የምንለው እንድ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦች ገንዘብ አዋጥተው ለተወሰነ አላማ እንዲውል ሲያደርጉና ሲመዘግቡ ነው። ሌላው በዚህ መልክ የሚቋቋም "ትረስት" የሚባለው ነው። "ትረስት" ተብሎ የተቀመጠውን ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲያውለው የተፈቀደለት አካል በአግባቡ ካልተጠቀመበት ወይም አይጠቀምበትም ብሎ ካሰበ መልሶ የሚወሰደው ነው። አመራሩን የመሰየም፣ የመሻም የባለገንዘቡ ስልጣንና መብት ብቻ ነው" በማለት ምላሽ ሰጥቷል።

ወላጅን ቁምነገር ሪፓርተር ጋዜጣ እንዲህ በማለት ጠየቀ፣

"በሀገራችን ሊንደውመንት ሲባል በስፋት የሚታወቀው ሌፈርት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣናት እነ ሌፈርት ሊንደውመንት መሆናቸውን በአንደበታቸው ለረጋገጠዋል። ለእዚህ ድርጅቶች እንዲመዘገቡ ጠይቃችኋል?"

እቶ ጌታቸው እንዲህ በማለት አሰደማሚ መልስ ሰጠ፣

"ምንስ አገባንና!

ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የፍትሕ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ዴሬክተር እንደገለጠው ኤፈርት የሚባል በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ አላከናወነም። በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ መሰረት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከአንድ አካባቢ በላይ ከሆነ በፌደራል ደረጃ የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው። ተመዝግበውም ሆነ አከብረው መንቀሳቀስ ያልቻሉትን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የመሰረዝ ስልጣን አለው። ይህ በ1952 ዓ.ም የወጣውና ቡተግባር ላይ ያለ ህግ የበጎ አድራጎት ድርጅት (መያድ) ትርጓሜ፣ ድርጅቶቹን ማን እንደሚመዘግብ እና እንደሚያፀድቅ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት ተጠቃሚዎች ማን፣ የበጎ አድራጎት የሚቀርብበት (የሚሰረዝበት) ሁኔታ የሐሳብ ማጣራት መቆጣጠር... ወዘተ ያጠቃለለ ነው።

ወደ ትርጓሜው ስንመጣ የ1952 ህግ "የበጎ አድራጎት ተግባር" ምን እንደሆነ እንደሚከተለው ይገለጣል፣

"የበጎ አድራጎት ድርጅት ተግባር ማለት የአንድ ሰው ሀብት ወይም ብዙ ባለሀብቶች ትርፍ ለማግኘት ሲይሆን በማይመለስ አኳኋንና ለህዝአለሙ አንድ የተወሰነ የጠቅላላ ጥቅም ማብ ላለው የሚያውልበት ሰራ ነው።"

ከዚህ የህጉ አባባል መረዳት የሚቻለው ነገር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች (መያዶች) ትርፍ ለማግኘት የተቋቋሙ አይደሉም። ገቢና ትርፍ በሚያስገኝ የንግድና ኢንቨስትመንት ሰራዎች ላይ መሳተፍ አይችሉም። መያዶች አንድ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦች ገንዘብ አዋጥተው ለተወሰነ አላማ ብቻ እንዲውል ሲያደርጉ አንጂ ለትርፍ የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ትርጓሜውን ስለማያሟሉ ሊመዘገቡም አይችሉም። ይህንን አውነት አያወቁ የአቶ መለስ ሆነ የአንጃው ቡድን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በሀገሪቱ ህግ መሰረት ኤፈርት በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ተመዝግቧል በማለት ይናገራሉ። ደግነቱ የተባረሩትም ሆነ በህወሐት ውስጥ ያሉት አመራሮች ለህዝብ በሚናገሩና በሚጽፉ ሰዓት የሚናበቡ ባለመሆናቸው የተጣረሰ እና አርስ በራስ በሚደባደቡ ሀላቦች የታጨቁ ናቸው። በአገሪቱ ህግ መሰረት መያዶች ለትርፍ የሚቋቋሙ አይደሉም ብሎ ሲያቡቃ እነሱ "ከኢንዶውመንቶቹ እንቅስቃሴ በሚገኘው ትርፍ" በማለት ይጽፋሉ።አሁንም የሀገሪቱ ህግ

"ለአንድ የተወሰነ ጥቅም ማብ ላለው የሚውልበት" ቢልም አነሱ "እንደ ባለሀብት ተቆጥረው" በማለት ይጽፋሉ። ይናገራሉ።

ወደ ምዝገባ ስንመለስ ደግሞ በ1952 ዓ.ም በወጣው ህግ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት (መያድ) በግዴታ መመዝገብ እንዳለበት ይደነግጋል። በዚህ ህግ ከፍል አንድ ቁጥር ሰባት ላይ "የአሰተዳደሩ ከፍል ነገሩን ማጽደቅ አለመፈለጊ ስለመሆኑ" በሚል ርዕስ ሰር፣

"የበጎ አድራጎት ድርጅትን ተግባር የአገር ግዛት ሚኒስቴር ካላፀደቀው በስተቀር ለይቋቋምም። የአገር ግዛት ሚኒስቴር ውሳኔ ከመሰጠቱ ቢራ አስፈላጊ ሲሆን ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚመለከታቸውን የሌሎች ሚኒስትሮችን ሐሳብ ይጠይቃል" በማለት ይገልፃል።

በተመሳሳይ መልኩ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲፀድቅ የሚቀርበው ጥያቄ ምን መምሰል እንደሚገባው በዚሁ ከፍል አንቀጽ አራት ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፣

"የበጎ አድራጎት ድርጅት ተግባር እንዲጸድቅ ለማድረግ የሚቀርበውን ጥያቄ መሰረት በህይወት ካለ መሰራቾ ራሱ ወይም ወኪሉ ካልሆነ በቀር ሌላ ሰው ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም። ...ለበጎ አድራጎት ተግባር ፍቃድ የመጠየቅ ግዴታ የሚወድቅባቸው ሰዎች ፈቃዱን ሳይጠይቁ የቆሩ እንደሆነ የተባለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ጽሁፍ እንዲፀድቅ የሚያቀርበውን ጥያቄ መሰራቾ ከሞት በኋላ በሦስት መር አቅቤ ሕግ መይም ማንኛውም ባለጉዳይ ሊያቀርበው ይችላል" በማለት ይገልፃል።

ከላይ ከተጠቀሱት የአገሪቱ ህግ መሰረት ኤፈርትን የመሳሰሉ በጎ አድራጎት ድርጅት የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ተቋማት ቢፈይሉ ደረጃ ምዝገባውን እንዲያከናውን ሰልጣን በተሰጠው መ/ቤት ቀርበው መመዝገብ አበረባቸው። "አስራት ግዘዉ መታሰቢያ" የሚባል አዚህ ግባ የሚባል የፋይናንስ አቅም የሌለው፣ ያውም ከደብረብርሃን የማይሻገር ድርጅት በተመዘገበበት ሁኔታ አገር አቀፍ እንቅሲቃሴ የሚያደርገው ኤፈርት በፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ከፍል አልተመዘገበም ማለት የህጉወየኑን ደረጃ ፍንትው አድርጎ የሚያመላክት ነው። ኤፈርት ማማሸ ጽ/ቤቱን አዲስ አበባ ባደረገበት፣ እንደ ጉና ያሉ ድርጅቶቹ ማዕከላቸው አዲስ አበባ በሆነበት፣ ጥሬ ኢቃምቾንና ማዕድናትን ከወሰዶ የኢትዮጵያ ከፍሎች በሚወሰዱበት፣ _ከትግራይ ክልል ወጪ ባሉ እንዳንድ አካባቢዎች ኘልማት ሰራ" እየሰራ ባለበት (በኦሮሚያና ደቡብ መንግድ ሰርቷል)

እንደ እንግሊዝ ባሉ የአውሮፓ ሀገሮች የንግድ ተጭማች ባለቤት በሆነበት ሁኔታ ባዩት ሚኒስቴር እንዳልተመዘገበ ማወቅ ለለሚው ግራ የሚያጋባ ነው።

እዚህ ነጥብም ላይ ቢሆን የህወሓት ታጋይ ባላስልጣናት እርስ በራስ የሚጋጭ መረጃ የሚሰጡበት ሁኔታ ታይቷል። አቶ መለሰ ኤፈርት የት እንደተመዘገበ ሳይገልጥ በደፈናው ሸሚ ተመዘግቦ ህጋዊ በሆነ ሁኔታ እንደሚንቀሳቀስ ይናገራል። ሽማግሌው ሰብሃት ነጋ የኤፈርት በሚ የት እንደተመዘገበ ባይገልጥም የውስጥ አና የውጭ አዲት እንዲሁም የኦፊሰሮች ሪፖርቱን በየጊዜው ለመንግስትና ፍትህ ሚኒስቴር እንደሚያቀርብ ተናግሯል። ለሁሉም ግልጽ እንደሆነ የፈደራል መዋቅር የሆነው ፍትህ ሚኒስቴር ያልተመዘገበውንና አውቅና ያልሰጠውን አካል አዲትም ሆነ ሪፖርት መስማት አይችልም። ያልመዘገበውን አካል ከመያድ ትርጉሞና ጦ ውጭ እየተንቀሳቀሰ ነው የሚልበት ሁኔታ አይኖርም። ሰለዚህ የሰብሃት ነጋ አነጋገር እንባጓሮን ከተመለከትነው ኤፈርት በፈደራል ደረጃ በፍትህ ሚኒስቴር ማህበራት ማደርኛ ተመዝግቧል የሚል ትርጉም ይሰጠናል።

ከሸማግሌው ሰብሃት ነጋ ቡተቃራኒ የቆመውና ምናልባትም አደጋውን በመገንዘብ ሽማግ አድርጎ የካደው ስየ አብርሃ ነው። እንደ ሰዩ አገላለጥ ከሆነ ኤፈርት በሀገሪቱ ፍትሕቤቶር ሀ መሰረት የመመሰረቻ ጽሑፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ለትግራይ ክልል አቅርቦ በዛው መሰረ የተመዘገበና እውቅና ያግኘ ድርጅት መሆኑን የገለፀበት ነው። ሁለቱ የእንድ ወቅት የኤፈርት ቁ ስራ አስፈጻሚዎች አንደኛው በፈደራል ደረጃ ተመዝግቦ ለመንግስትና ፍትሕ ሚኒስቴር አዲት ሪፖርት ያቀርባል ይላል። ስዩ ደግሞ ኤፈርት ህጋዊ ሰውነት ያገኘው በፍትሃብሔር ሀ መሰረ በትግራይ ክልል ነው ይላል።

ስዩ አይደረስብኝም በማለት የቸሸበት የራሱ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች ይኖሩታል። እዚህ ቅጥፈቶች ከማንዛቤ አጥረት የመነጩ ሳይሆን ሆነ ተብሎ በታቀደና በተዘጋጀ ሁኔታ የተሠ ናቸው። በአንድ በኩል ለኤፈርት ህጋዊ ሰውነት የሰጠው የትግራይ ክልላዊ መንግስት እንደገ መግለጽ ሚስጥሩ ተጠብቆ እንዲኖር አድል ይሠጣል። የትግራይ ክልል በምንም መልኩ የኤፈርት ገመና በማጋለጥ ህጎውጥ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚፈልግበት አንዳችም ህጢናዊ ሁኔታ ሊኖር አይችልም። ሁኔታዎች እየገፉ ከመጡም የትግራይ ክልል ቀድሞ የተዘጋጀ ቦማስመሰል ለህ የህጋዊነት ሰርተፊኬት ማዘጋጀቱ የማይቀር ሀቅ ነው። በመሆኑም ከለሱ ስዩ የትግራይ መንግስ

ኢኮኖሚያዊ ምንጩ የሆነውን ኤፈርት ማጋለጥ ስለሆነ ቀሚሞክረው አይደለም። በሌላ በኩል ለዚ ኤፈርት በትግራይ ከልል ሀጋዊ ሰውነት ተሰጥቶታል ብሎ ሊጽፍ በቀጣይ ኤፈርት የሚያጋጥመውን የህጋዊነት ጥያቄ እንዲሸገረው በማሰብ ነው። ነገ የሚመጣው መንግስት እንዲሸገረው በማሰብ ነው። ነገ የሚመጣው መንግስት ኤፈርትን አስመልክቶ ከህጋዊነት ጀምሮ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሞኖፖላይዝድ ያደረገበትን አሠራር መፈተሹ የማይቀር ነው።ህገ-ወጥነቱን ከረጋገጠም አርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህም "ወዲ ኦብርሃ" የኤፈርት እንቅስቃሴ ህገራዊ መሆኑን እያወቀም ቢሆን እወናብዶ ለማለፍ ፈለገ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የኤፈርትን ህጋዊ ምዘገባ በተመለከተ ወላፈኑት መውሰድ ያለብለገው ገብሩ አስራት ነው። ገብሩ አስራት በመጽሐፉ ላይ ኤፈርት ትግራይ ይመዘገብ ወይንስ ፈደራል መሆቀስ እልፈለገም። በበጎ ለድራጎት ሀጉ መሳረት ሕጉ የሚጠይቀውን መሰ ሰሙሉ ለሚልቶ ተመዝግቧል ለማለትም አልደፈረም። ይልቁንስ ሐላፊነቱን ለመከለጠት የፈለገው ሲሉ ባለሞያዎች ነው። እነዚህ የህግ ባለሞያዎች ኢትዮጵያዊ ይሁኑ ኤርትራዊ፣ ህንድ ይሁኑ ፓኪስታን፣ ቻይና ይሁኑ አሜሪካዊ በገብሩ አስራት የተገለጠ ነገር ባይኖርም የሰጡትን ተቆማ መቀበላቸውን በመጽሐፉ ያመላክታል። የህግ ሙያተኞች ጠቅመውን ኤፈርት የበጎ ለድራጎት ድርጅት እንዲሆን ወሠንን በማለት ይናገራል። የኤፈርት ህጋዊ ማዕቀፍም በዚህ መልኩ ምላሽ እንዳገኘ ይገልፃል። ታዲያ እውነት ወይት እለየ_የኢጋጣሚ ነገር ሆኖ በ2001 ዓ.ም የበጎ ለድራጎትና ማህበራት አዋጅ ከፀደቀ በኋላ የኤጀንሲው ቁና ሰራ አስኪያጅ አጅግ የቅርብ ጓደኛዬ የነበረው አሊ ሲራጅ ሆን። ነበሱን ይማረው፣

ለማስታወስ ያህል አሊ ሲራጅ ቦመጀመሪያ ማስታወሻ በሆነው ማመሳከሪያ ቅኖዲዮጵ በርካታ ቦታ ተጠቅሷል። አሊ ሲራጅ ከምርጣ 97 በፊት በሊህዲግ ኦቦት ስብሃት ለገሰን ከንዜ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ ሆኖ ቦሚሰራ ነበር። በምርጫ 97 የኡይለ አበየ ህዝብ በመቃወሙ ኢጋጥ ሰቅለቅ ብሎ ለያለቀለ "የኡይለ አበየ ህዝብ ለምን ይጠላናል?" ብሎ ቢረትት ሰምኑን ሊደራ ነበር። ቢረከትም ለማስታወሻ እንዲሆነው "የህብት ምርጫዎች ውጥ ብሎ በጽኑመው የጽሁ መሳለት ጀምሬ ቦሚያሳየው መጽሀፉ ቢድጋሚ ለስለቅሳታል። በትግል አስት ኃይሎቹ ቦመሆኑ ለመገለጽ ጥሳልቆበታል። በለሊ ላይ ተረማምዶ ለሀዲሶቹን ነፃንት ሲፈቅሱ ለጋጭት ያመነጨት ሕሸፍባቸዋል።_እንደ እውነት ከሆነ ሲራጅ ሀጨላቶን ተመግቶ ሲሰርዶ መግቦ ይሌለበት ሰው ነበር። በድቲአይ መመሀርነቱ ቢቆጣል ይሸው እዚ ሰማንቶን ተጠቅሞው ,ለ ሳቅሙ

ሰማሽከም ለንደ ዶርዘ ንጠላ መሳሪያ ኮማራ ቀኝ ሲያላትመት ጨፈራውን ልጦ ሞት። ርጉጥ ከለራተኛ ክፍለ የህብረተሰብ መምህርነት ተንሰቶ ለንድ ጊዜ የኢህአዴግ ጽሀፍና የአቂ አገባ ካበደ.. ሌላ ጊዜ የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበራት ኤድዝ ሞና ዳሬክተርደ.ኖ ለላ ጊዜ የኢኮኖሚና ፋይናንስ ሚኒስቴር ዲኤታ ሆኖ መቀመጥ ይሉኝታ ላለው ሰው ግበጨት አይቀርም_

የሆንው ሆኖ ከሚች አለ ሲራጅ ጋር ጥሩ ጊዜ ለሳሲፈናለ። የበላይ ሆኖ አንዲበረደም የተሰጠውን አዲሱን የመያዶች ሀግ አዳራሽ ለአዳራሽ አየሔድን ለባላትና ህዝብን አደንቁናል። በዚህ አልበቃ ብሎ ታንዛኒያ ድረስ ቤመሔድ ለፍሪካ ወንድሞቻችን ለማስተማር ጥረት አድርገናል። ለፍሪካ ወንድሞቻችን የመያድ ሆኑን ለንቅጽ በለንቀጽ አየጠቀሱ ተሳልሳመናለ ይህም ሆኖ የመያድ ሀግ በተንሳ ቁጥር ታንዛኒያ (ለንዜባር) ትዝ ተለኛለች። ታንዛኒያ_የበርያ ንጽ የተካሔደባት "የቢጋማዬ" ሀገር!_ታንዛኒያ... ለመድሐኒት በሚል ሰው ለውን አየገደለ ያሚለባት ሀገር! የተበዳይለ የለው ሰጋ ያሚታይቦት ሀገር!_ የተፈጨ ለንጀት በብልቃጥ ያሸጠባት ሀገር!_የአልቢናስ" የሰጋት ኦሮና ያልደረቀ የደም ለምባ!_ ታንዛኒያ_የቅዳሜው ሐሲለሰለ ሁሰተኛ ደረጃ ትበቤት!...ታንዛኒያ ብዙ ያሚወራላት ሀገር! የሳ ሰው ይበለን።)

ወደ ቀደመው ጉዳያችን ስንመለስ ከበን ኤድራትትና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ይሬክተር ከሆነው አለ ሲራጅ ጋር የጠበቀ ግኑኝነት ነበርን። ኤጀንሲው የበን ኤድራትት ደኒጅቶችን የሚመዘግብ፣ የሚቆጣጠርና የሚሰርዝ በመሆኑ በኢ.ህአዴግ/ ህወሓት ለይን ትልቅ ትኩሶት የተሰጠው ነው። የኤጀንሲው የሳምንት አንቅስቃሴ በቅጥታ ለበረከት ስምአንቷ... በሬክት ደግ ለአቶ መለስ የሚያቀርብበት አለራር የተዘረጋለት ነው።

አንሆ፣ ከአለታት በአንዱ ቀን ሸማግሌው ሰብሃት ነጋ የአሜሪካ አማርኛ ድምጽ ለይጀ ከሆነው ጋዜጠኛ ጋር አዲስ አበባ ቀርረ። ኤፈርት በሀግ የተመዘገበ ድርጅት መሆኑን ተጠየቁ "እቶ እንደልቡ!" ኤፈርት በህግ የተመዘገበ በን አድራትት ድርጅት ከመሆኑም ባሻገር ለመንግስትና ለፍትህ ሚኒስቴር በየጊዜው ሪፖርት እንደሚያቀርብ ገለጠ። በሰሙየው መግለጫ የተደናግጦ የኢሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ከምሁራንና ከህዝቡ ለሚመጣብን ጥያቄ አለቀርቦ ለመዘጋጀት እንዳረዳን መረጃ ማሰባሰብ ጀመርን። ለኔ የተሰጠኝ ተልእኮ አለ ሲራጅ በመሔዱ ኤፈርት በበን አድራትት ድርጅትነት የተመዘገበበትን መረጃዎች ይዞ መምጣት ነበር

የተቀበልኩትን ሐላፊነት ለመወጣት ወደ ጓደኛዬ አሊ ሲራጅ ቢሮ በእካል ሔድኩኝ። ኤፈርት በበጎ አድራጎትነት የተመዘገበበትን ማስረጃና ለትረፍኬት እንዲያሳኝ ጠየኩት።

ለቅስቀ ብሎ ሲያለቅስ ያየሁት አሊ ከትከት ብሎ ሳቀብኝ። በመገረም እየተመለከተኝ እና ለሜን እየጠራ፣

"አቦ! የእኛ መስሪያ ቤት ለትርፍ የሚሰራ ነጋዴ አይመዘግብም። የማታውቅ ከሆን እስከ 2001 ዓ.ም. የመያድ አዋጅ እስኪወጣ ድረስ በሰራ ላይ ውሎ የነበረው የ1952 ዓ.ም. የፍትህብሔር ህጉና በ1959 ዓ.ም. የወጣው የሚህበራት ምዝገባ ደንብ ነው። በአዋጁም ሆነ በደንቡ ላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢና ትርፍ የሚያስገኝ ስራ ላይ መሰማራት እንደማይችሉ ይደነግጋል። ይሆን ህግ የማያከብሩት ሁኔታ ከተፈጠረ ሙሉ ለሙሉ ይሰረዛሉ። መያዶች ለትርፍ የሚሰሩ ከሆን ከነጋዴ በምን ይለያሉ?" በማለት ማልሶ ጠየቀኝ።

በአሊ ሲራጅ ምላሽ በጣም ተደናግጬ፣

"እና ምን እያልከኝ ነው?" በማለት ጠየኩት።

በድጋሚ ተንከትክቶ እየሳቀ፣

"አቦ! መጀመሪያ ድመቷ ጣራ ላይ ወጣች!... ቀጥሎ እያ_ኩ የማስረጻህ ካድሬ አልመሰልከኝም። ከተማ ቀመስነቱ የት ጠፋ?" በማለት መልሶ ጠየቀኝ።

ፊቴን ኮስተር አድርጌ፣

"የአባጅፋር ልጅ ለስራ ነው የመጣሁት። የምጠይቅህን በስነ-ስርዓት መልስልኝ" አልኩት።

ለምን እንደሆነ ባላውቅም አሊ ሲራጅን የታላቅ ወንድሜ ያህል አወደዋለሁ። ትህትናውና አመለ ሸጋነቱ ከልቡ ጋር የተጣበቀ ነው። ሌብነት የሚባል በአካባቢው አያልፍም። በምርጫ 97 "አርከበ መራሽ መንግስታዊ መሬት ወረረ" ወቅት በአርከበ አቋቢይ ግፊት እንዲት መሬት ወስዶ ነበር። ዘግየት ብሎ በተደረገው ማጣራት አስቀድሞ ጥፋቱን በማመን የወሰዳትን መሬት መልሷል። በድጋሚ ስቅስቅ ብሎ አልቅሷል። የአዲስ አበባ ህዝብም መጫም ቢሆን ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር ታርቆ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ እንደሌለ ተገልጦለታል።

አሊ ሲራጅ በቁንታው ፊቱን አጨማደ፣

"አቦ፣ ነገርኩህ እኮ። አስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ በበጎ አድራጎት ላዋጅ ላይ የገቢ ማስገኛ የሚከለክል አንቀጽ በመኖሩ ምክንያት ኤፈርት በመያድነት አልተመዘገበም። አደግመዋለሁ፣ ኤፈርት የበጎ አድራጎት ድርጅት ትርጓሜን አያሚላም። ለአስራ ምናምን አመታት ኤፈርት ኢንዶውመንት እንደሆነ የተጻፈው ውሸት ነው" በማለት ምላሽ ሰጠኝ።

ዘላለም እየተታለልን መኖራችን ቁጭት ውስጥ ከቶኝ፣

"አሊ! ታሪክ መስራት አለብህ። ይህን ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሳየት ይኖርብሃል። አስከጫቲ ድረስ..."

ከማለቴ አቋርጦኝ፣

"ምነው አልሞትልህ አልኩኝ እንዴ?" በማለት ተናገረ። በሚያሳዝን መልኩ ታመሰከተኝ።

አጅንዳ ቀይረን ስለሌሎች ጉዳዮች ተነጋግረን ተሊያየን።

አነሆ! ከእለታት በአንዱ ቀን በስደት ቤቴ ውስጥ ሆኜ ማህበራዊ ድረገፅ ስከፍት የሚያስደንግጥ ዜና ተመለከትኩ። ሚኒስትር ዴኤታ አሊ ሲራጅ በድንገተኛ ህመም ከዚህ አለም በሞት መለየቱን በምስል ተደግፎ አየሁ። በጣም አዘንኩ። ባልጠበኩት ሁኔታ አንባዬ ወረደ፣ ለአንድ አሊ ብቻ ሳይሆን አህዴድ ውስጥ ለሚገኙ ብዙ "አሊዎች" አለቀስኩ።

የአሊ ሲራጅን ዜና አረፍት ከተመለከትኩ ከጥቂት ወራት በኋላ አንዲት አብራን የሰራች ካድሬ አፈላልጋ አገኘችኝ። ከብዙ ጨዋታዎች መሐል በአሊ ሞት ማዘኔን ነገርኳት። እሷም እንዳዘነችና ከሞቱ በኋላ የነበረው ሁኔታ ይበልጥ አንዳስቆጫት ነገረችኝ።

ለካስ! የአሊ ሲራጅ የቀብር ስነ-ስርአት እና የአዝን ፕሮግራም የተፈፀመው በአባላት እና የአካቢው ህዝብ መዋጮ ነበር። በመኖሪያ ቤቱ ከተቦካ የቡሀቃ ሊጥ ውጪ ምንም አልነበረም፣ ምንም!!

ክፍል 4

“ትልማና ማረሻ!”

“መንገድ ተሰራ ሲባል ሕዝቦች የሚገናኙበት፤ አንዱ የአንዱን ባህል የሚማርበት ዕድል ሠፋ ወይም ተፈጠረ ማለት ነው። ስለዚህም የትብብርና የእስተሳሰብ ሉድማሱ ሮሚሰፋበት ዕድል አለ ማለት ነው። የውሃ አገልግሎት ተሠራ ማለት ያቺ ምስኪን ሴት አራት አምስት ሰአታት ለውሃ የምታጠፋውን ጊዜ ትቆጥባለች ማለት ነው። ጤና ኬላ ተሠራ ማለት ጤንነቱ የተጠበቀ ልጅ መማር ይችላል ማለት ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መከፋፈት ማለት አከ ለዲሞክራይታዜሽን ሰፊ ምንጣፍ እየተነጠፈ ለፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚሆን ጊዜ አገኙ ማለት ነው። በአህጉሪ ማህበረ- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው እየተቀየረ ነው። ፖለቲካዊ ፍላጎቱ የሚጨምር ትውልድም እየተፈጠረ ነው።”

ታጋይ ጀኔራል አበበ ተከለሐይማኖት

ሪፖርተር ጋዜጣ ግንቦት/2008 ዓ.ም.

ምዕራፍ 15

ታሪካዊ መነሻና ተልዕኮ

ህወሓት በሰኔ ወር 1985 ዓ.ም. "አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎቻችንና ቀጣይ ተግባሮቻችን" በማለት ያወጣው ሠነድ ላይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሐይሎች ብሎ ሶስት አደረጃጀቶች መግለጹ የሚታወስ ነው። ከእነዚህ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ልዕልና (ሔጂሞኒ) በቁጣይነት ሊያረጋግጡ ይችላሉ ከተባሉ ሐይሎች ውሲጥ አንደኛው "ማህበራት" ሲሆኑ፣ እነዚህ ተቋማት የፓርቲው አንዱ ክንፍ ተደርገው ይወሰዳሉ። የማህበራቱ አጠቃላይ አቅጣጫዎችና ስራዎቻቸው የሚቀረጹት በፓርቲው ነው። ፓርቲው የአገሪቱ ሁኔታዎች ለማህበራቱ አንዲመች አድርጎ የሚቃኝ በጣም ሰፊና ስልታዊ የአፈፃፀም አቅም የሚጠይቅ ስራ ይሰራል። በአንድ በኩል የጎንዘብ አቅማቸውን ሰማይነጥፍ ሁኔታ እንዲጎለብት በሚያስችል ሙሉና ሁለንብ ድጋፍ በመስጠት የሚፈፀም ነው። በሌላ በኩል በሚፈጠርላቸው የጎንዘብ አቅምና በራሳቸው ተነሳሽነት በሚያገኙት ፋይናንስ ማህበራዊ መሠረታቸውን የሚደግፉበት ሁኔታ ይመቻቻል።

ፓርቲው ማህበራቱ በሚፈልገው መንገድ እንዲንቀሳቀሱ የተለያዩ አሠራሮችን ይከተላል። ከእነዚህም ውስጥ አመራሮቻቸውን ከመመደብ ጀምሮ አባላት የመመልመልና የማሰልጠን ስራ ይሰራል። ስልጠናዎቹ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርሆዎችና አሠራሮች የተቃኙ በማድረግ ማህበራቱ በፖሊሲዎቹ፣ በስትራቴጂዎቹና የአፈፃፀም መንገዶቹ ላይ ግልፀኝነት ፈጥረው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ነው። ማህበራቱ በተለይም አመራሮቹ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ የፓርቲው መርህ በሆነው ማዕከላዊነት በመሆኑ አውቀታቸው የሚታጠረው ተሰክቶ በተሰጣቸው ነገር ብቻ ነው። የማህበራቱ አመራሮች ወደ አባላት ሲወርዱ በተመሳሳይ የሚያስተጋቡት በማዕከላዊነት የተሰበኩትን ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ ይሆናል።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ህወሓት በጎደፈው ፓሊሲ መሠረት ማህበራት ግዙፍ የሆኑ የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተልዕኮዎች አላቸው። አቶ መለስ በጻፈው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መሰመሮችና ስትራቴጂዎች" በሚለው መጽሐፍ ማህበራት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በህብረተሰቡ ውስጥ ገዢ አመለካከት እንዲሆን ታሪካዊ ተልዕኮ አላቸው በማለት ይገልፃል። ማህበራቱ አጅግ የበዛውን ህዝብ ያቅፋሉ የሚል ታሳቢ ስለተወሰደ ህዝቡን ወደዚህ አቋም ማድረስ የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር ይገባቸዋል የሚል አመለካከትም ነበረው። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት ለማምጣት ማህበራት የማይተካ ሚና እንዳላቸው በተሰይጥ ጊዜ በፃፉት መጽሐፍትና አንደበት የሚጠፉ አይደለም።

አቶ መለስ "የዴሞክራሲ መሠረታዊ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሀፉ ላይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት ተረጋግጧል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ይገልፃል፣

"የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብን የበላይነት ማረጋገጥ ማለት በጣም የሚበዛውን የህብረተሰብ ክፍል ስለማንኛውም ለይነት ጥያቄ ብቻውን ሆኖ በነፃነት ሊያስብ በሚችሉ ያሉት መሠረታዊ አምነቶች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስለሆኑ ዙር ዙር ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስቻለ መድረስ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት የሚመጣው አንድ ሰው ከሃሳቡ ጋር ሙሉ በሙሉ ከተዋህደው አመለካከት ውጪ ማሰብ ስለማይችልና ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አፀድ የማይወጣ በመሆኑ የሚመጡ ናቸው። በጣሙን የሚበዛው የህብረተሰብ ክፍል አዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት ተረጋግጧል ሊባል ይችላል" በማለት ይገልጻል።

በመሆኑም በህወሓት/ኢህአዴግ ከንፍነት የሚደራጁትና የሚንቀሳቀሱት ማህበራት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት እንዲመጣ ታግተው ይሰራሉ። ሶሚያድጉት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ስራዎች አያንዳንዱ ሰው ሲያስብ "ከአዶ መላስ" አስተሳሰብ ማዕቀፍ እንዳይወጣ የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል። ህብረተሰቡን በኢኮኖሚያዊ ጥቅም ቀይዶ መያዝ፣ የትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ መንገድና ሌሎች አገልግሎት የሚሉ ተጨማት

በመስራት፤ የብድርና እራጣ አገልግሎት መሰጠት፤ በተከታታይ ስብሰባ በመጥመድ ማህበ የኢብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት እንዲያመጣ ይተጋሉ። ይህ የትድግያ ትደግፍ ተልዕኮአቸው ነው።

ህወሓት የሚመራቸው ማህበራት ሁለተኛ ተልዕኮ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሚና በመቀነስ ገዢውን ፓርቲ የሚረቅ፣ የሚስተካከልና በኢብዮታዊ ዴሞክራሲ ጥላ ስር ሰመሆን ችግርን የመፍታት ነው። ማህበራቱ አባላቶች በኢብዮታዊ ዴሞክራሲና መሰረታዊ መርሆዎች በመመራት ስርአቱ አደጋ ሲገጥመው ተጠላልፎ ወደ ጠቅላላ ቀውስና መበታተን እንዳይገባ ግንጋርድ ሆነው የሚያገለግሉት ናቸው። አብዮታዊ ዴሞክራሲያውዊ ግንባሩ (ህወሓት) የሚፈጽማቸው ስህተቶችና ጉድለቶች የማህበራዊ መሠረቱን እምነቶችን እየሸረሸሩ ወደ ፀረ-ህወሓት እንዳይመሩት ንቁነት የሚያደርጉ እና የሃይል ሚዛኑን የሚጠብቁ እንዲሁም የሚያርሙ ናቸው።

"አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎቻችንና ቀጣይ ተግባሮችን" በሚለው ሠነድ ላይ "ማህበራቱ ካድሬ ሲፈጽሙው የሚችለውን ጉድለት ብዙም ሳንርቅ በእነሱ ተፅእኖ እንዲያሙ ያደርጋሉ። የካድሬዎቻችንን ዝቅጠት የሚገታ ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ" በማለት ሚናቸውን በግልጽ ያስቀምጣል። በነገራችን ላይ እኖ መለስ ማህበራቱ የተቃዋሚዎች ሚና ይተካሉ ብሎ የገለፀው በኢትዮጵያ ምድር ለተራዘመ ጊዜያት (በትንሹ 40 ዓመት) በህ ውድድርም ቢሆን ወደ ስልጣን የመምጣት እድላቸው ዜሮ ነው የሚል ሃሣብ ስለሚያራምድ ነው። ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ህወሓት/ ኢህአዴግን በማንኛውም የፖለቲካ ሃይል መተካት የሚቻልበት ተጨባጭ ሁኔታ እንደሌለ የፅና እምነት አለው። የህወሓት/ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ለረጅም ጊዜ የተበታተኑ፣ ደካሞችና ሠፊ የድጋፍ መሰረት ስለሌላቸው ለተራዘሙ ዓመታት የገዢው ፓርቲ መተኪያ ሊሆኑ የማይችሉና በዚህም መቀጠላቸው የማይቀር እንደሆነ ይናገራል። ታሪክ ከተቃዋሚዎች የሚጠበቀው ተልዕኮ በእጅጉ ደካማ በመሆኑ አማራጭ መንገድ መፈለግ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል። ይሄ አማራጭ (ማህበራትን ማጠናከር) ህወሓት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪው እንዳይጠፋ ቀጭድዶ የሚይዝ ታይል (አደረጃጀት) ሲሆን እንደሚገለፅ ይገልፃል። እንደዚህ አይነት ቀጭዳጅ ታይል ከለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪን ጠብቆ ለመሔድ እንደሚያስችል ያመላክታል። ይህን በተመለከተ "የዴሞክራሲ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፉ ላይ፤

"...ተቃዋሚዎች በጥቃቅንቸውም ሆነ በአደረጃጀታቸው ሊሀአዴግን ለመቃወም ይህ ነው የሚባል ሚና መጫወት የሚችሉ አይደሉም። ስለዚህ እኛ እንደፈለግን እንዳንሰርቅ፣ እንደፈለግነው መብት እንዳናፍን በሌላ አንጋር ለብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪያችንን እንዳናጠፋ ቀፍድዶ የሚይዘን ሃይል የለም። እንደዚህ አይነት ቀፍዳጅ ኃይል ካለ ባህሪን ጠብቆ ለመሄድ ምቹ ነው። እንደዚህ አይነት ልጓም በሌለበት ጊዜ ግን ባህሪን ጠብቆ ለመሄድ ለይቻልም ባይባል እንኳ በአጅጉ ከባድ ነው" ይላል።

አቶ መለስ ተቃዋሚዎች በነፃ ውድድር እንኳን ወደ ስልጣን የመውጣት እድል ስለሌላቸው ሌላ አማራጭ ያስፈልጋል ያለበት አገላለጥ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡

"...በምንገኝበት አገራዊ ሁኔታ ሊሀአዴግን በማንኛውም ሌላ የፖለቲካ ኃይል መተካት አይቻልም። መደባዊ አሰላለፍ አስኪቀየር (ኢንፓወርመንት ፕላኑን ልብ ይሏልን) ድረስ ያለ አማራጭ አንድም ሊሀአዴግ ባህሪውን ጠብቆ ይቅጥላል፤ አሊያም ስውለው በስብሶ ወደ ቦናፓርቲዝም በዚያም በኩል ወደ አገሪቱ መቧታቱን ያመራል። ተቃዋሚ ኃይሎች በሌሉበትም ሆነ በምርጫ ሊሀአዴግን ተክተው አገሪቱን አስተባብረው ለመምራት የሚያስችላቸው ተጨባጭ ሁኔታ የለም። ...የሊትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃ ውድድር ወደ ሰልጣን የመውጣት አድላቸው በተጨባጭ መደባዊ አሰላለፍ ዝማ ያደርገዋል።... የሊትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የአኛ አይያዝ ከቋፐር ሳይገባ ለረጅም ጊዜ የተበታተኑና ደካምች፣ የሊሀአዴግ መተኪያ ሊሆኑ የማይችሉና በዚህም መቀጠላቸው የማይቀር ነው። ታሪክ ከነዚህ የሚጠብቀው ተጨባጭ በጣም ደካማ ነው" ይለናል።

በአቶ መለስ አምነት በኢትዮጵያ ምድር የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር መከተል የህልውና ጥያቄ እንደሆነ፤ ኢትዮጵያ ይህንን መስመር ካልተከተለች የመቧታቱን እና የእርስ በራስ አልቂት እንደሚያጋጥማት፤ ህዝባችንን ከአጠቃላይ ቀውስና መበታተን ለማዳን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች (ማህበራት፣ አብዮታዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች) ልዩና መተኪያ የሌላው ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ ያስገነዝባል። እነዚህ ሐይሎች ግዙፍ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም መገንባት እንዳለባቸው ያሳስባል። ይህን አቅም እየተጠቀሙ በአገራችን ውስጥ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የአስተሳሰብ የበላይነት እንዲመጣ የማይተካ ታሪካዊ ሐላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል። በመሆኑም የሁሉም የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች መሰረትና መነሻ ወሳኝ

የሆኑለት ህዝብ ጥቅሙ እንዲጠበቅለት ማድረግና ከሱ በተቃራኒ የቆመ ማህበረሰብ ላይ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ እጽንኦት ይሰጣል።

በሌላ በኩል አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባሰቀመጠው "የእቀራረብ ማሻሻያ" መሰረት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በአብዮታዊ ማህበራት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚመሩበት ሁኔታ በመሆኑ እርስ በራስ መተሳሰር ይኖርባቸዋል። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች የሚመጋገብና የተሳሰረ ከፍለ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችላቸውን ደረጃ እስኪደርሱ "ኢኮኖሚክ ኢንስትሩመንት" የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይፈጠራል። ወከለነዋል የሚሉት ህዝብ ወደ ቅሬታ ጉበቡ ሰርአቱን እንዳያንገዳግድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቱን የሚስተንፈስ ሰራ ይሰራሉ። በውሃ፣ በጤና እና ማህበራዊ አገልግሎቶች በመሳተፍ አሰላለፉን ወደ እነሱ ያደረገውን አካል ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ። ይህን ጥቅም እየሰጡ ማህበረሰቡን የማደራጀት፣ ተቀባይነት የማሳደግና በሌላው ላይ የበላይነት የማረጋገጥ ግባቸውን ያሳካሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ማህበራትን የመሰሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የህወሓት "ቁልፍ የፕሮፖጋንዳ አውታሮች" በመሆን ማገልገል እንደሚገባቸው በሰነዶቹ ላይ በዝርዝር እንዲሰፍር ተደርጓል። አደረጃጀቶቹ በነፃ ማህበር ስም ስለሚቋቋሙ ህዝቡን የማነሳሳትና በእጅ አዙር ከስርአቱ ጋር እንዲሰለፍ የማድረግ ተልዕኮ ይኖራቸዋል። ህዝቡን በነፃ አደረጃጀት ስም እየጠሩ በሚያደርጉት የውይይትና ከርከር መድረኮች በተለያየ መልኩና አግባቦች የስርአቱን አስተሳሰብ የሚያሰርጹ ይሆናሉ። ይህን በተመለከተም "አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎችንና ቀጣይ ተግባሮቻችን" በሚለው ሰነድ ገጽ 64 ላይ፣

"ህዝባዊ ማህበራትና አደረጃጀት የተግባር ማስፈፀሚያ መሳሪያ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው። ከዚህ ጋር ተዛምዶ ስለ ልዩ ልዩ ነጥሮች የሚወያይና የሚከራከር መድረኮች በመሆን አስተሳሰብ ይቀርፃሉ። ስለሆነም ቁልፍ የፕሮፖጋንዳ አውታሮች ናቸው። አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሳሰብ ልዕልናን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ህዝቡን ለደራጅቶ በልማት ተግባር ላይ ለማሰማራት ያገለግላሉ። ...አንሱን አስተሳስሮ በማንቀሳቀስ፣ ሰፊው ህዝብ አላማዎችን እንዲፈጽም ከማለባሰብና ለማለማረት አንዲሁም የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ልዕልና በዘላቂነት እንዲመጣ ማድረግ ይችላሉ። የፐሮፖጋንዳ ስራችንን በምናከናውንበት ጊዜ ማን የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ዋንኛውና ውጤታማ ፕሮፖጋንዳ ተግባርንና አሱን

ሰራት ለድርጎ የሚካሔድ ማብራሪያና ውይይት ነው። ሁሉም ለውታሮቻችን ይሆን ዘንድ መመሪያው መውሰድ አለባቸው በማለት ይገልጻል።

ለዚህ ነው በህወሓት የተፈጠሩና በየጊዜው እንዲጠናከሩ የተደረጉ ማህበራትን ለንቃኝ ለሙታዊ ዴሞክራሲ አላማዎች ጋር አስተሳስረን መመልከት የሚኖርብን። ማህበራቱ ሚኖራቸው ራዕይ፣ ተልዕኮና ስትራቴጂካዊ ተግባራት ከፓርቲው ህልውና ጋር የተጣበቀ በመሆኑ ነጻና ጉዞ ከሌላው ነጥሎ ማየት አይቻልም። የትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ)፣ ማህበረ ስኳት ትግራይ (ማረት)፣ የትግራይ ሴቶች ማህበርና የትግራይ ወጣቶች ማህበርን በዝርዝር ማጥናት ፍላጎት ያለው ሰው ከህወሓት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አላማዎች ጋር ደርቦ መመልከት ያስበታል። እነዚህ ማህበራት ለብቻቸው በነፃነት የቆሙ ሳይሆኑ እንደ አንድ የህወሓት ርጅታዊ መረብ የሚቆጠሩ ናቸው። ርግጥ ነው ማህበራቱ የህወሓት አንጻጽ ከንፍ መሆናቸው ሳታወቀ ለማህበረሰቡ በተለይም ግራ ቀኙን በአግባቡ ለማይመለከተው ሷለም አቀፍ ማህበረሰብ ሠለቲካው ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው አደረጃጀቶች ተደርገው ይቀርባሉ።

ተልዕኮአቸውም በትግራይ ማህበራዊ ፍትህ ከማምጣት አንፃር ብቻ ተለይቶ እንዲቀርብ ይደረጋል። ሌላው ማህበረሰብ ተቋቋሙበት ከሚባለው አላማ ውጭ ብዙውን ጊዜ ሀገውጥ በሆነ ሳኔ እንደሚሰራ አይነገረውም። እነዚህ ድርጅቶች በኢትዮጵያ በሌሎች ከፍሎች ባልታየ ሁኔታ ከውጭ መንግስታት ጋር የአርዳታ ውል ይፈራረማሉ። ከአሜሪካን ተራድኦ ድርጅት (USAID)፣ ከአውሮፓ ህብረት (ዩህ)፣ ከዩኒሴፍ፣ ከጂቲዜድ፣ ከሲ.አር.ዲኤ፣ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር አርዳታና የፐሮጀክት ውል ይፈራረማሉ።... ጥያቄው ለምን አሮሞ ልማት ማህበር (አልማ) እንደዚህ አይነት ስልጣን አልተሰጠውም?... ጥያቄው የደቡብ ልማት ማህበር (ደልማ) ለምን ከውጭ ሀገራት ጋር የሚደራደርበት ስልጣን የለውም?... የህላዌ ዮሴፍ የግል ንብረት የሆነው አማራ ልማት ማህበር (አልማ) ለምን በተናጠል መንግስትን ወክሎ አይደራደርም? ወዘተ የሚሉት ናቸው። ለነገሩ ዲንሸና ወንዶ በህይወት አሉ ወይ ተብሎ የተጠየቀው ወደ አልማ እና ደልማ ትመልሶ የሚነሳ ጥያቄ ይሆናል።

ምዕራፍ **16**

ማህበረ- ረድኤት ትግራይ (ማረት)

"ማረት የተረቆተውን የተፈጥሮ ሀብት ለንዲንከባከብና ለንዲያለማ፣ በዕለት ደራሽ ሴራ ለንዲሰማራ ተደርጎ ከሙጭ ሊጋሾች የሚገኘውን ለርዳታ ሊያሰተባበረ በአገሪቱ ሕግ መሰረት መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሆኖ ተመዘገበ።"

ገብሩ አስራት
ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

"ዩኒሴፍ ለብዛናውን ትኩረቱን ወደ ትግራይ ያደረገበት ምክንያት የትግራይ ክልል መሪቶች በአግባቡ የተደራጁና ከድርጅታችን ጋር የተሻለ ግንኙነት መፍጠር በመቻላቸው ነው"

የዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ተጠሪ
የአፍሪካ ቀንድ መስከረም 1986

***

ማህበረ ረድኤት ትግራይ (ማረት) ሲቋቋም የነበረው ዋነኛ አላማ የትጥቅ ትግል ለሚያካሂደው ህወሓት ቀጥተኛ ለርዳታ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆነውን የአለም አቀፍ ህብረተሰብ በመንግስታዊ ያልሆነ በጎ ድርጅት (መያድ) ሰም በመቅረብ ለርዳታ ማሠባሰብ ነበር። ህወሓት በምዕራቡ አለም በተለይም በአሜሪካን የሚገኘው "ሴንትራል ዳታቤዝ" በአሸባሪነት የመዘገበው በመሆኑ በቀጥታ የውጭ ለርዳታ የሚያገኝበት አድል በጣም ጠባብ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ህወሓት የሚከተለው ማርከሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ (ማሌሊት) ርዕዮተ አለም ከምዕራባውያኑ በተቃራኒ የቆመ በመሆኑ ሊያጠፋት አሊያም ፖሊሲውን እንዲቀይር በማሰብ ህወሓትን ፊት እንደሚነሱት የታወቀ ነው። "የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይውደም!" የሚል መፈክር ያነበው የአልባኒያው ኮሚኒስት ግለባጭ የሆነውን ህወሓት ሲ.አይ.ኤ ከምድረገፅ ሊያጠፋው ቢሞክር ሊያስገርም የሚችል አይደለም። ለአሜሪካን ከደርግ ይልቅ ህወሓት ጠላቱ ነው።

በሌላ በኩል ህወሓት ያሠማራው ሰራዊት መጥሮ አንዲቀጋና በህይወት አንዳቆይ አህል ለማስፈልማል። የትግራይን ህዝብ በማሰገደድ በውንብድና አና በግብር መልኩ የሚቀበለው ሰራዊቱ ቀለብ የሚበቃ አይደለም። ሌሎች አንደ አልባሳት ያሉ ሰብአዊ ቁሳቁሶችም ያስፈልጋሉ። ስለ ለጥንካሬው መሰረት አድርጎ የወሰደውን የትግራይ ህዝብ ለማጣል የሚያስችል ስራ መጣል አለበት። የትግራይን ህዝብ በማንኑቱ፣ በመሬቱና በስብዕናው መደፈር ቱጅትና ለማስገበት ህወሓት የሚፈጥረው ታሪክ በባዶ እጅ ከሆነ ትርኑም አልባ ፕሮፖጋንዳ መሆኑ ለቀርም። በትግራይ ህዝብ ዘንድ ህወሓት ተቀባይኑት ለማግኘት ከሚያስፕው አርዳታ የምግብ ይዞ ማድረግ ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል።

ይህንን ታሳቢ በመውሰድ ህወሓት በተመሰረተ በአራት አመቱ (በ1970 ዓም መጀመሪያ) ማከቡ ሪድኤት ትግራይ (Relif Society of Tigray- REST) የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አቋቋመ። ማህበረ ጠቀሜታዎችን በሚያስገኝ መልኩ አንዲቀጥር ተደረገ። በአሳማ ሲሸም ከአለም አቀፍ ማህበረሰቡ አርዳታ በማሰባሰብ የህወሓትን አቅም ማጠናከር ከሚያስፕው ረዳታ የተወሰነውን ለትግራይ አርሶአደሮች የምግብ ድጋፍ በማድረግ ፖለቲካዊ ድጋፍ ማበስብ፤ የምግብና አልባሳት አርዳታውን አንደ ካሮትና ዱላ በመጠቀም የትግራይ ገበሬን ለቁጣጠር፤ ከታጋይ ሰንቅና ድጋፍ ከሚለው በመቀነስና መልሶ በመሸጥ የጦር መሳሪያ ግዥ ማናወን... ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው።

ማረት ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይም ለምዕራባውያን ገለልተኛ ሆኖ የተደራጀ ማስመሰል ጥረት ቢደረግም ድርጅቱ አመራር የሚሰጠው ከህወሓት ፖሊት ቢሮ አባላት ነው። ድርጅቱ ስራ አስፈፃሚዎች የሚመረጡትም ከህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ የተሻሉ ሚባሉትን በመለየት ነው። አባይ ፀሀዬ፣ ገብሩ አስራት፣ ተክለወይኒ አሰፋ ከድርጅና አመራር ሰት የሚጠቀሱ ናቸው። በሱዳን፣ በእንግሊዝና አሜሪካን ህወሓትን ወክለው ቢሰሩ የነበሩት ሳነ ኪዳኔ (ጃማይካ)፣ አብደይ ዘርአይ፣ ሐይሌ ኪሮስ አና ብርሃኔ ገ/ክርስቶስ በሚሪት አንክኒሳቴ ላይ ቋልፍ ሚና ነበራቸው። በትጥቅ ትግሉ ወቅት የህወሓት የፀጥታና ስለላ ሀላፊ የነበረው አንዱ ሃመድህን፤ የህወሓት የውጭ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ ሰዩም (መንፍን) ማዘጋጀ ሪድኤት ትግራይ(ማረት) በውጭ ሀገር የሚሰራው በቅርብ ይከታተሉ ነበር።

አነዚህ ከፍተኛ የህዉሓት አመራሮች በውጭ ሀገር ድጋፌ አደረጃጀቶችን በመጠቀም አለም አቀፍ የእርዳታ ሰጪዎችን፣ ባለስልጣናት እና ጋዜጠኞችን የማሳመን ስራ ሠርተዋል። እርዳታ ሰጪዎቹን ልዩ ማብሪያ በሙጥራት ያልተሰራውን እንደተሰራ አድርጎ በማቅረብ ተጨማሪ እርዳታ እንዲለግሱ አድርገዋል። የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በከፍተኛ ደሞዝ በመቅጠርና አንሶላ በመጋፈፍ ለህዝብ ያልታደለውን እህል እንደተሰራጨ፣ ያልተሰራውን ለወክን እንደተሰራ፣ ያልተቆፈረ የውሃ ጉድጓድ እንደተቆፈረ አድርገው የዜና ዘገባና ሀተታ እንዲሰሩ አድርገዋል። የተዘጋጀውን አልምጭ የተቀናበለ ቁጥር የያዘውን ሪፖርት እርዳታ ሰጪዎቹ እንዲደርሳቸው አመቻችተዋል። በተሰያየ ጊዜያትም ሪፖርቱ ታትሞ ለምዕራባውያን በመሰጠት ለጋሾች የሠጡት እርዳታ በትክክለም ለህዝቡ መድረሱን እንዲያመላክታቸው ተደርጓል።

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ማህበረ ረድኤት ትግራይ (ማረት) ከአለም አቀፍ እርዳታ ሰጪዎች ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት የማይዋሹት ነገር የላቸውም። በአንድ በኩል የተረጂውን ቁጥር ለማለደግ እንዲያስችላቸው የትግራይን ህዝብ ብዛት አዛብተው ያቀርባሉ። በሌላ በኩል አንሳኝና ነጋዴ ቦኩ በመቅረብ የተገኘውን እህል መልሰው መላልሰው ይሸጣሉ። ለምሳሌ ያህል ማረት የትረጂውን የትግራይ ህዝብ ቁጥር ለማሳደግ ለተከታታይ አስር አመታት የህዝቡን ቁጥር 5 ሚሊዮን አካባቢ ያቀርብ ነበር። በ1986 ዓ.ም በተካሔደው የህዝብ ቆጠራ የትግራይ ህዝብ 3፡1 ሚሊዮን መሆኑ በይፋ ቢገለጥም ማረት ለአለም አቀፍ እርዳታ ሰጪ ሀገሮች ከ5 ሚሊዮን በላይ ብሎ ማቅረቡ ተጨማሪ እርዳታን ለማግኘት አስችሎታል። በተለይም አስከፊውን የ77 ረሃብ ወቅት በማስታከክ ህውሃት ብሎም ማረት በቅጋር በተመታው ህዝብ ስም በመነገድ ከፍተኛ ገንዘብና አለማ ግከማቸት አስችሎአቸዋል።

የህወሓት/ማረት ታጋዮች ነጋዴ በመምሰል እህሉን እየተመላለሱ በመሸጥ የገዘሉ አቅማቸውን ማሳደጋቸውም ተመሳሳይ ነዉ። የህወሓት ቱይናንስ ኃላፊ የነበረው ጉቦረመድህ አርአያ በተለያዩ ሚዲያዎች የሰጠው መግለጫ ይህንን መረጃ የሚያጠናክር ነው። በካድሬነት ዘመኔ አብሬ የሰሯቸው የህወሓት ታጋዮች የገብረመድህን ማስረጃ ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጠውልኛል። የቱይናንስ ሀላፊው ከህወሓት በደረሰው መመሪያ መሰረት ስሙን "መሐመድ" በማለትና ራሱን ወደ ነጋዴነት በመቀየር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ሊድር ድቱ ገቢ አድርጓል። ይህንን በተመለከተ "ታላቁ ሴራ" በሚል መጽሐፍ ላይ ገ/መድህን እንዲህ በማለት ሁኔታውን ከገፅ 36-37 ይገልፃል፣

"ለአርዳታ የመጣውን እህል የወያኔው አባሎች ነጋዴ መስለው እየቀረቡ ይገ/መው እንደሚሸጡት አኔም አቶ መሐመድ የሚል መጠሪያ እንደነበረኝ ከዚህ ቀደም ገልጫለሁ። ይህ ነገር ሲነሳ የታወሰኝ ጉዳይ አለ። አንድ ከርሰቲ የምትባል በሱዳን የምትኖር አንግሲዛዊት አለች። አርዳታ ሰጪዎች ይዛ መጣች። ለእኔ አሰቸኳይ ትዕዛዝ ተሠጠኝ። "እህል ይደረደርልሃል ልብስህን ለውጥና ነጋዴ መስለህ ሽጥ" የሚል። ከዚህ ቀደም እንደገለጽኩት መሐመድ ተብዬ የትውልድ ሃገሬን ተንቤን ብዬ ለሸጥኩት እህል 3 ሚሊየን ተቀብያለሁ። በ1967 አራት ሚሊዮን ይዘው የመጡ ፊረንጆች ነበሩ። ተከዜ ወንዝና በሊሎችም አራት ቦታዎች በመቆ የሚቆጠር ኩንታል ተደርድሮ ተሸጠላቸው።"

ከላይ እንደገለጥኩት ገ/መድህን ለህዝብ ያቀረበው መረጃ ምንም አይነት የተጋነነ ነገር እንደሌለው አብረውት ከነበሩት የቀድሞ ታጋዮች ማረጋገጥ ችያለሁ። በተለይ ሙላይ ማሰልጠኛ ጣቢያ ከነበሩት ዲሞብላይዝድ ታጋዮች ውስጥ "ምፅላል ገ/ሚካኤል" እና ሊታይ ኪዳኔ" የሚባሉ ተማሪዎቼ ካቲካላ ሽያጮና የቤት ውስጥ ሰራተኛ በመምሰል በመግባትና መሸጡ ይደት እንደተለተፉ በክብር የሚያነሱት ነው። በኢህአዴግ ቢሮ የሰራ ባልደረባዬ የነበረው ታጋይ ይሳቅ ቆሪጥ ከርሰቲ የተባለችውን የእንግሊዝ ጋዜጠኛ በቅርበት እንደሚያውቃት አጫውቶኛል። ከርሰቲ ዋነኛ ስራዋ ለማህበረ ሬድኤት ትግራይ (ማረት) መኪል በመሆን ካመጣቸው አርዳታ ገንዘብ ውስጥ እስከ ህያ በመቶ ኮሚሽን የምትወሰድ ነበረች። ቁጥር የተቀቀለበትን ሬፖርት ለአርዳታ ሰጪዎቹ የማድረስ ሃላፊነትም በእሷ እና አሷን በመሰሉ ፈረንጆች ላይ የወደቀ ነበር። ከህወሓት አመራሮች ጋር አንሶላ ትጋፈፍ እንደነበር ጨምሮ አጫውቶኛል።

የማረት ሌላኛው የፋይናንስና ቁሳቁስ ምንጭ የመንግስት ንብረቶችን መውረስ ነው። ህወሓት በጦርነት አሸንፎ ከተቆጣጠራቸው አካባቢዎች የሚወለደውን የህዝብ ንብረት ከፈሉ የሚተላለፈው ለማረት ነበር። በተለይም ከግብርና ከትምህርት፣ ሆስፒታል፣ ውሃ ልማትና ሌሎች መንግስታዊ ድርጅቶችን ንብረት በመውረስ የራሳቸውን ፕሮጀክቶችና ፕሮጄክሮች በመቅረፅ የቁሳቁስና የገንዘብ አቅማቸውን አጎልብተዋል። በጦርነቱ ሊጋጭ ይችኛውን የሰቲነና የምስክ የጄነትና መጓጓዣ ትራንስፖርቶች በመቀማት የግል ንብረታቸው አድርገዋል። ከእህል አቶፍ የአርዳታ ድርጅቶች የሚመጣ እህል፣ መድሐኒትና ሌሎች የህክምና መሳሪያዎች ያመላለስቢታል።

ዘፌ ኤፈርትና ትልማ (ትግራይ ልማት ማህበር) ለተሰማሩበት የትራንስፖርት ዘርፍ አየጨነት ማፈጋገሜ የወሰዱት ከማረት እንቅስቃሴ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

በአጠቃላይ መልኩ በድርቅ ለተጎላው የትግራይ ህዝብ ከውጭ አርዳታ የሚመጠትን አህሎች፡ አልሚ ምግቦች፡ ጨርቃጨርቅና ሌሎች ቁሳቁሶች መልሶ መላልሶ በመሸጥ፡_ ከሊዲየ ጋር፡ ከደርግ ጋር ከህወሓት ባለንጣዎች ጋር ወግነዋል የተባሉ የትግራይ ተወላጅችን መሬትና ከብት በመቅማትና ከፍተኛ ግብር በመጣል፡... የህዝብ፡ የመንግስትና የግል ባለሀብቶችን ንብረት በመውረስ የተጠናከረው ማረት ለህወሓት ቁልፍ የፖለቲካ ሰራ ማስኪያ ቦታ ነበር። ሰፖርቲው አመራሮችም ለመገናኛ፡ የውጭ ሀገር ጉዞና የህክምና አገልግሎት ወጪ የሚሸፈንው ማረት በዚህ መልኩ የሰበሰበውን ገንዘብ ነበር። ጉበረመድህን እርእያ እንደገለጠው ከሆነ የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባሉና ከድል በኋላ የትግራይ ከልል ፕሬዝዳንት የነበረው ጉብሩ አሰራት የልብ ህክምና ሰሜድሪግ ወጭ ሀገር ሲሔድ 40ሺህ ዶላር በጥሬ ገንዘብ ተመድቦ የህክምናው ወጪው እንዲሸፈን ተደርጓል። ጉበሩ አሰራት የማረት፣ ትልማና ኤፈርት ጉዳይ ሲነሳ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ የሚንዘረው እንዱ ምክንያት ይሔ እንደሆን የሚነገረው በዚህ ምክንያት ነው። አርማጭሆ በሚሊዮን የሚጠጉ የትግራይ ተወላጆች ቢድርቅ ምክንያት አንደ ቅጠል አየረገፉ ባለበት ሰዓት 40 ሺህ የአሜሪካን ዶላር የርዳታ አህል ተሸጠ የተገኘን ገንዘብ እንዲታከምበት የተፈቀደን ድርጅት ሰም አለመጠበቅ የበሉበትን ወጪት እንደ መሰበር ይቆጠራል። በሌላ በኩል "ለሱበለዊ አርዳታ የመጣውን ብዙ ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን አህል፡ አልሚ ምግቦችና መድሐኒቶች እየተሸጡ ለህወሓት ግጠናከሪያና ሰር መሳሪያ ማሸሮ ይውሉ ነበር" የሚል የአምነት ከሀደት ቃል ከጉበሩ አሰራት ሙጠበቅ የቁህት ይሆናል። ጉበሩ በምንም መልኩ ቢሆን ለትግራይ ህዝብ የመጣን የምግብ አርዳታ ቁሳቁስ ሸጠን ለጦር መሳሪያ መግዣ አውለነዋል ሊል አይችልም። ፈረንጅ የትግራይ ህዝብ በረሃብ መርዙን ተመልከቱ ለምኖ ያመጣውን አርዳታ ህወሓት የትግራይን ህዝብ ለመከፋፈልና ተቃውሞውን ለመቆጣጠር አውሰት እንደነበር መመስከር አላፋሪ ከመሆኑም በላይ የታሪክ ተጠያቂ ማድረጉ የማይቀር ይሆናል። አሰከግንባኝ ድረስ ለአቶ ጉበሩ አስራት ትልቁ የህይውቱ ውርደት በትግራይ ህዝብ የታሪክ ተጠያቂ መሆን ነው።

***

ህወሓት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ማህበረ ረድኤት ትግራይ (ማረት) በጎ እድራጎት ድርጅት መሆኑና በሀገሪቱ ህግ መሰረት መመዝገቡን አወጀ። ምዝገባ ያደረማውና ህጋዊ ሰውነቱን

ያለው ከአይጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን (አመዝኮ) መሆኑን አሳውቋል ማረት ይሔን ይበል እንጂ በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግ መሰረት ሀገር በቀል የሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን (መያዶን) ለመመዝገብና ፍቃድ የመሰጠት ስልጣን በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የማህበራት ማደራጃ ይሆናል ማለት ነው። በተጨማሪም ማረት በበጎ አድራጎት ህጉ መሰረት መመዝገብ የሚያስልባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። በ1952 የፍትሐብሔር ህጉ መሰረት ግብረሰናይ ድርጅቶች ትርፍና ገቢ የሚያስገኙ የንግድና ሌሎች ኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ መሳተፍ አይችሉም። የንግድ ፍቃድ ወስዶ ግብር እየከፈለ የሚነግድና ኢንቨስት የሚያደርግ ንጋዴ ባለበት ሁኔታ በተመሳሳይ ዘርፍ ላይ መያዶች ይሳተፉ ማለት ፍትሐዊ አያደርገውም። የህጉ መሻሻል ሃሳብ ይህ ነው። ተመሳሳይ ንግድና ኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርቶ እንደኛው ግብር የማይከፍል፣ ለለኛው የሚከፍል ከሆነ የመወዳደሪያ ሜዳው እኩል መሆን አይችልም።

ይህም ሆኖ ማረት ከአይጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን (አመዝኮ) ጋር እንዲጣበቅ ጥያረገበት የራሱ ምክንያቶች አሉት። አመዝኮ ከአለም አቀፍ እርዳታ ከሚሰጡ ሰጋሽ ሀገራት ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት አለው። መንግስትንና ለጋሽ ሀገራትን እንዲሁም መንግስትንና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን በህግ ቁተሰጠ ስልጣን አገናኝ ሆኖ የሚያገለግል ነው። አመዝኮን መቆጣጠር ማለት በሌላ አንጋገር እርዳታ የሚሰጡ ሀገሮችንና ድርጅቶችን በቁጥጥር ስር ማዋል ይሆናል። ለጋሽ ሀገራት እና እንደ ዮኒሴፍና የአሜሪካን ተራድኦ ድርጅቶችን በማሳመንና ተጽእኖ በማሳደር ፕሮግራማቸውንና ፕሮጀክቶቻቸውን በተፈለገው ቦታ እንዲያውሉ እድል ይከፍታል።

ማረት ከሀውሓት የፖለቲካና የድርጅት ስራ ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ መጀመሪያ የተደረገው የቦርድ አባላቱንና እደረጃጀቱን ማስተካከል ነው። የቦርድ አባላቱ በፓርቲውና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች እንዲካተቱበት የተደረገበት ነው። በዚህ አሳቤ መሰረት የማረት የቦርድ አባላት አባይ ፀሀዬ (የቦርድ ሰብሳቢ)፣ ገብሩ አሰራት (የትግራይ ፕሬዝዳንት)፣ ዶ/ር ሰለሞን እንቋይ (የትግራይ ክልል ማህበራዊ ጉዳይ ሃላፊ)፣ ዶ/ር ሙሉ ቀፀላ (ዩኑይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ም/ሚኒስትር)፣ ዶ/ር ኢትዮጵያ በየነ (የፓርላማ አባል) እና ታጋይ ተክለ ወይኔ አሰፋ (የማረት ዴሬክተር) ናቸው። ከቦርድ አባላቱ ስብጥር መረዳት እንደሚቻለው ህወሓት አሎኝ ብሎ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቅሳቸው ሰዎች የተካተቱበት መሆኑን ነው። ከዚህም በተጨማሪ የቦርድ አባላቱ "ትግራይ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በልዩ ሁኔታ በደል ስለተፈፀመባት ልዩ ጥቅም ሊታገኝ ይገባታል" ብለው የሚያምኑ ናቸው። ቡሳይ እንደ አባይ

ፀሃዬ፣ ገብሩ እስራትና ዶ/ር ሰለሞን እንዳይ አደነት ታጋዮች ለትግራይ እየተደረገ ያለው ሌ
ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የትላንት በደልን ለማክሰል እንደሆነ ያለምንም መሸማቀቅ
በተደጋጋሚ የሚናገሩበት ነው። እነዚህ ታጋይ ባለስልጣናት ከበረሃ ጀምሮ በሚያዘጋጇት
የኢንጾክትሪኔሽን ሰነዶች ያለፉት መንግስታት ትግራይን ነጥለው በደል እንዳደረሱባት፣ ትግራይ
ወደ ፍፁም ድህነት የሔደችው ባለፋት መንግስታት ሆን ተብሎ በታቀደ ሁኔታ በተቀየሰ ፖሊሲ
መሆኑን፤ ከትግራይ ከልል የሀብት ዝርፊያ ተካሂዶ ሌላው አካባቢ እንዲበለጽግ መደረጉን
የሚያመላክቱ ናቸው። ከድል በኋላም ይሄን አስተሳሰባቸውን በግላጭ ለማራመድ የሚሸሿቸው
ሰዎች አይደሉም። የትግራይን መበደል፣ መጨቆን፣ መደህየት፣ መዘረፍና ሌንዱስትሪ አልባ መሆን
ከሰሜን ሸዋ፣ ከአርሲ፣ ከደብረማርቆስ፣ ከወሊጋ፣ ከሱማሌያ፣ አፋር፣ ቤንሻንጉል... ወዘተ ጋር
ማወዳደር አልቻሉም። አይፈልጉምም።

እንግዲህ እንደዚህ አይነት የተዛባ አእምሮ ያላቸው ታጋይ ባለስልጣናት የማረት ሸርድ
አባላት ሲሆኑ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ለመገመት ብዙ የሚያስቸግር አይደለም። ቢያንስ
የትግራይ ህዝብ በታሪኩ አይቶ የማያውቀውን አንዲመለከት በሌላው ላይ ተጽእኖ ማሳደራቸው
አይቀርም። ትላንት ደረሰ ያሉትን በደል ለማክሰስና ተጠቀመ ያሉትን ደግሞ ለመበደል በሙሉ
አቅማቸው የሚሯሯጡ ይሆናል። ...ለዚህም ነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ1200 ፕሮጀክቶች በላይ
ለትግራይ ከልል ቀርበው ወደ ተግባር የተቀየሩት። ...ለዚህም ነው የአርዳታ ሴቪ ሀገሮችና
ድርጅቶች የሚለጠጡን እህል ለማከማቸት በመቀሌ ከተማ ታይቶ የማይታወቅ የምግብ ማከማቻ
ዘመናዊ ጎተራ የተዘጋጀው። ይህ በማረትና ትልማ ቅንጅት የተሰራው ጎተራ (ማከማቻ መጋዘን)
በአንድ ጊዜ ከ450ሺህ ኩንታል (45ሺህ ሜትሪክ ቶን) የማከማቸት አቅም አለው። ህወሓት ይሄን
የምግብ ክምችት ለከፉ ጊዜና ለ"ምግብ ለሰራ" ፕሮግራም ይጠቀምበታል። ጎተራው እናዳይሟጠጥ
ደግሞ የፌደራል መንግስቱን እርዳታ ማስተባበሪያ (ለመዝኮ) ታማኝ በሆኑ ታጋዮች ቁጥጥር ስር
እንዲውል አድርጓል። የኢህአዴግ ባለስልጣናት እንደሚገልጡት የታጋይ አባዲ ዘሙ ወደ አመዝኮ
የመሔድ ምክንያት ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።

ማረት ከላይ የተገለጠውን ተልእኮ እንዲፈጽም ለማስቻል ቁልፍ የህወሓት ታጋይ
የሆነውን አባዲ ዘሙ የአመዝኮ ምክትሚሽነር እንዲሆን አደረገ። አባዲ ዘሙ ማረት ከተመሰረተ
ጀምሮ ህወሓት አዲስ አበባን እስከተቆጣጠረበት (1983 ዓ.ም) ድረስ ለ13 አመታት ዋና
ዴሬክተር ሆኖ የሰራ ነው። የመንግስት ለውጥ በተደረገ በማግስቱ የአመዝኮ አናት ላይ ተቀመጠ።

ሠላሾት ብሎም የኤፈርት ምክትልና ዋና ሰራ አስፈፃሚ ሆነ። ታጋይ አባዲ ዘሙ የማረትና ኤፈርት ከፍተኛ አመራር ከመሆኑም በተጨማሪ የአንዳንዶቹ ኩባንያዎች የሼር ባለቤት እንዲሆን ተደርገል። ከእነዘህም መካከል የትግራይ ከልል ፕሬዝዳንት የነበረው ጉብሩ አስራት ባለቤት የሆነችው ተጋዳሊት የውብማር አስፋው የ36 ሚሊዮን ብር ሼር ባለቤት የሆኑቸበት አልመዳ ጨፖታጨርቅ ይገኙበታል። የውብማር ሼሯን ለኤፈርት በስጦታ መልክ ሰጥታ ብትወጣም አባዲ ዘሙ በባለቤትነት እንደቀጠለ ነው። ታጋይ አባዲ ከአልመዳ በተጨማሪ ብርሃነ ኪሚካል፣ የመሰባ ሀነፃ መሳሪያዎችና ሼባ ቆዳ ፋብሪካ አከሲዮን ባለቤት ነበር።

ህወሓት ሰልጣን በተቆጣጠረ በቀናት ውሰጥ ታጋይ አባዲ ከማረት ተነስቶ ጨፒ መንግሲታዊ ተቋም የሆነው አመጣኪ ሲመጣ ሃሳቡና ዋና አላማው ቶሎ ቶሎ ሀብትን ለማካበትና ለማደለብ የሚያስችለው የሀብት ማመንጫ ቢታ መሆኑን አስቀድሞ በመረዳቱ ነው። በሌላ አነጋገር አመጣኪ በአብዘኛው የተሰጠው ሃላፊነት በአንድ በኩል ከውጭ ሀገራትና ድርጅቶች ጋር የሚያገናው በመሆኑ ብዙም ለአይታና ተጠያቂነት ምሚመቹ አይደለም። በሌላ በኩል ሲጋቭ ሀገራቱና አርዳታ ሰጪ ድርጅቶቹ በሚሰጡት ድጋፍ አሳበው የሲቭራል ፖሊሲያቸውን አንዳያራምዱ ቁጥጥር ለማድረግ በማበብ ነው። ለሁሉም ግልጽ እንደሆነው ሁሉ ህወሓት በሌላው ዓለም የሌለ የራሱ የሆነ በሚስጥር የተያዘ የፖለቲካ ሰሌትና አቋም ያለው በመሆኑ በምዕራባውያን እንዲታወቅበት አይፈልግም። ህወሓት በኢደባይ የብዙሃን የፓርቲ ስርዓትና ነፃ ገበያ ኢኮኖሚን እንደሚኩተል ለአለም አቀፍ ተቋማትና ሀገሮች መላልሶ ቢናገርም በተጨባጭ ፀረ- መድብለ ፓርቲና ነፃ ገበያ መሆኑ ቦተገለጠ ነው። ከበረሃ ጀምሮ ይህንን የሚያውቁት እንደ አከሰፋምና ዩኒሴፍ ያሉ አርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፣ ህወሓት ስልጣን ከጨበጠ በኋላ የፖለቲካ እቋሙን በመሞ ሰሚኒያ ዲግሪ እንደተለወጠ እንዳያምኑ የሚያደርገው ህወሓት አመጣኪን የመሳሰሉ መንግስታዊ ተቋማት በቁጥጥሩ ስር ከዋለ ነው። ከፊትና ከኋላም አባዲን የመሳሰሉ ታጋይ ባለስልጣናት ማበማራት ከትትሉን የተጠናከረ እንዲሆን ያደርገዋል።

እንደተጠበቀው ታጋይ አባዲ ዘሙ ከአለም አቀፍ አርዳታ ሰጪዎች የሚመጣውን ድጋፍ በሚዘገንን ሁኔታ ወደ ትግራይ ማጋዘ ጀመረ። የውጭ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አይናቸውን ትግራይ ላይ እንዲተክሉ በርካታ የልማት ፕሮጀክቶችና እቅዶች እንዲያርሉቸው አደረጉ። ህወሓት "ምጣብ ለስራ" በሚባለው ፕሮጀክት ውስጥ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጅች እንዲታቀፉ ሰትራቴጂ ነደፉ። በትግራይ ከልል የተጠቀሰው "ምጣብ ለስራ" ስያሜው ለርቶ